# ምዕራፍ አንድ

## ጠቅላላ

### አንቀጽ ፩

### አጭር ርእስ

ይህ ቃለ ዓዋዲ "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን አንድነትና አስተዳደር ለማጠናከር በ፲፱፻፺፩ ዓ.ም. ለሦስተኛ ጊዜ ተሻሽሎ የወጣ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ቃለ ዓዋዲ" ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል፡፡

### አንቀጽ ፪

### ትርጓሜ

፩. "የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ" ማለት፦

ሀ) በአጥቢያ ደረጃ ለተቋቋመውና ለሚቋቋመው የቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) የሚያስፈልጉትን አባላት ለመምረጥና በአባልነትም ለመመረጥ የሚችሉ ቤተ ክርስቲያንን በሀብታቸውና በአገልግሎታቸው የሚረዱ ካህናት፣ ምእመናንና የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች የሚገኙበት የሰበካ ጠቅላላ መንፈሳዊ ጉባኤ ወይም የአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ካህናትና ምእመናን ስብሰባ ነው፡፡

ለ) በወረዳ ደረጃ ለተቋቋመውና ለሚቋቋመው የወረዳ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ የሚያስፈልጉትን አባላት ለመምረጥና ለመመረጥ የሚችሉና የሰበካውን ሀብትና አገልግሎት የሚያስፋፉና የሚቆጣጠሩ ከእያንዳንዱ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የተወከሉ ካህናት፣ ምእመናንና የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች የሚገኙበት የወረዳው ሰበካ ጠቅላላ መንፈሳዊ ጉባኤ ነው፡፡

ሐ) በሀገረ ስብከት ደረጃ ለተቋቋመውና ለሚቋቋመው የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ የሚያስፈልጉትን አባላት ለመምረጥና ለመመረጥ የሚችሉና የሰበካውን ሀብትና አገልግሎት የሚያስፋፉና የሚቆጣጠሩ ከእያንዳንዱ ወረዳ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) የተወከሉ ካህናት፣ ምእመናንና የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች የሚገኙበት የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ጠቅላላ መንፈሳዊ ጉባኤ ነው፡፡

መ) በመንበረ ፓትርያርክ ደረጃ ለተቋቋመው የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) የሚያስፈልጉትን አባላት ለመምረጥና ለመመረጥ የሚችሉና የሰበካውን ሀብትና አገልግሎት የሚያስፋፉና የሚቆጣጠሩ ከእያንዳንዱ መንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ የተወከሉ ካህናት፣ ምእመናንና የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች የሚገኙበት የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ (የሀገር አቀፍ አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ) ነው፡፡

፪. "የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ" ማለት በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን፣ በወረዳ፣ በሀገረ ስብከት፣ በአጠቃላይ በመንበረ ፓትርያርክ በየደረጃው በተቋቋሙትና በሚቋቋሙት ሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያት በየራሳቸው ጠቅላላ መንፈሳዊ ጉባኤ የሚመረጥና ለየራሳቸው ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር አገልግሎት የተሠየመ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ነው፡፡

፫. "የሰበካ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ" ማለት፦

ሀ) የገዳም መምህር (አበምኔት)

ለ) የደብር አለቃ

ሐ) ለገጠር ቤተ ክርስቲያን ዋና ኃላፊ ሆኖ የተሠየመ ቄሰ ገበዝ ወይም መሪጌታ ማለት ነው፡፡

፬. "ሥራ አስኪያጅ" ማለት፦

ሀ) የወረዳ ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ

ለ) የሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ማለት ነው፡፡

፭. "ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ" ማለት የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ነው፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## በየደረጃው የተቋቋሙትና የሚቋቋሙት የሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያት የወል ድንጋጌዎች

### አንቀጽ ፫

### የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ መቋቋም

፩. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ሥር ከመንበረ ፓትርያርክ እስከ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ድረስ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ በዚህ ቃለ ዓዋዲ መሠረት ተቋቁሟል።

፪. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ባለበት ቦታና እንደ ዚሁም የቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት በሚገኝበት ሁሉ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ እንዲቋቋም ይህ ቃለ ዓዋዲ ያስገድዳል።

፫. የታወቁና ታላላቅ የአንድነት (የመቁነን) ገዳማት ቅዱስ ሲኖዶስ በሚያወጣው የገዳማት አስተዳደር ደንብና መመሪያ የሚተዳደሩ ስለሆነ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ እንዲያቋቁሙ አይገደዱም። ሆኖም እንደ አካባቢውና እንደ አስፈላጊነቱ እየታየ ሊያቋቁሙ ይችላሉ።

፬. የተቀራረቡ አብያተ ክርስቲያናት ከተስማሙ በአንድ ሰበካ ጉባኤ ሊደራጁ ይችላሉ።

፭. ከአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ጀምሮ ከወረዳ እስከ መንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ድረስ በየደረጃው የተቋቋመውና የሚቋቋመው የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር ፫፻፺፰ እና ፫፻፺፱ መሠረት ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተሰጣት ሕጋዊ መብትና ግዴታ በቤተ ክርስቲያኒቱ ስም ይሠራበታል።

፮. የየሀገረ ስብከቱ መንበረ ጵጵስና ዋና ከተማ እንደ አንድ ወረዳ ስለሚቆጠር የራሱ የሆነ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤን ያቋቁማል።

### አንቀጽ ፬

### በየደረጃው የተቋቋሙትና የሚቋቋሙት የሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያት ጠቅላላ አቋም

፩. የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ካህናትና ምእመናን የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ፤
፪. የወረዳ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ፤
፫. የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ፤
፬. የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ።

### አንቀጽ ፭

### የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ዓላማ

በየደረጃው የተቋቋመውና የሚቋቋመው የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ዓላማ ቀጥሎ የተመለከተው ነው።

፩. ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ለመጠበቅና አገልግሎቷም የተሟላ እንዲሆን ለማድረግ፤

፪. የቤተ ክርስቲያንን አገልጋዮች በሐዋርያዊ ተግባር ለማደራጀትና እንደ ዚሁም ችሎታቸውንና ኑሮአቸውን ለማሻሻል፤

፫. ምእመናንን ለማብዛትና እንደዚሁም በመንፈሳዊ ዕውቀት ጉልምሰው በምግባርና በሃይማኖት ጸንተው በክርስቲያናዊ ሕይወት እንዲኖሩ ለማድረግ፤

፬. የቤተ ክርስቲያንን አስተዳደር ለማሻሻልና በማናቸውም ጉዳይ ራሷን ለማስቻል፤

## አንቀጽ ፯

## የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ተግባር

በየደረጃው የሚገኘው የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የተቋቋመበትን ዓላማ ለመፈጸምና ለማስፈጸም የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

፩. የእግዚአብሔርን ወንጌለ መንግሥት መስበክና ትምህርቱንም ማስፋፋት፤
፪. መንፈሳዊና ዘመናዊ ትምህርት ቤትን ማቋቋምና ማደራጀት፤
፫. መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎትን ለምእመናን ሁሉ ማዳረስ፤
፬. የሰንበት ትምህርት ቤትን ማቋቋምና ማጠናከር፤
፭. ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎትና ድርጅት የሚያስፈልጉትን ሁሉ ማሟላት፤
፮. የቤተ ክርስቲያን አስተዳደርና አገልግሎት በቅዱሳት መጻሕፍት መሠረት በሕግና በሥነ ሥርዓት መምራት፤
፯. ቤተ ክርስቲያንን በሀብትና በንብረት በኩል ራሷን ማስቻል፤
፰. የቤተ ክርስቲያን ሀብትና ንብረት እንዳይባክን፣ እየተመዘገበ እንዲጠበቅ፣ እንዲለማና እንዲያድግ ማድረግ፤
፱. ሕገ ቤተ ክርስቲያን በሚፈቅደው መሠረት ከበላይ የሚሰጡትን ሕግ ጋት፣ደንቦች፣መመሪያዎች፣ ትእዛዞችና ውሳኔዎች መፈጸምና ማስፈጸም፤
፲. በቅርብም ሆነ በሩቅ የሚገኙ ሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያት በማናቸውም ጉዳይ እርስ በርሳቸው ተባብረውና ተረዳድተው እንዲሠሩ የተቻለውን ሁሉ ማድረግ፤
፲፩. ልዩ ልዩ የምግባረ ሠናይ ድርጅቶችን ማቋቋምና አገልግሎታቸ ማሟላት፤
፲፪. የሕንፃ ሥራ ፣ እድሳት ፣ ጥገናና የመሳሰሉት ሥራዎች ሁሉ ጠብቀው የሚፈጸሙበትን እቅድና መርሐ ግብር ማዘጋጀት፤ በ መዋላቸውንም መቆጣጠር፤
፲፫. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከ ብዛት፥ የሰበካውን ገንዘብና ንብረት ገቢና ወጪ የመሳሰሉትንም ቲስቲካዊ መረጃዎች በወቅቱ እየመዘገቡ በሪፖርት እንዲገለጽ
፲፬. በዚህ ቃለ ዓዋዲ መሠረት ማናቸውንም ቤተ ክርስቲያንን የሚ ጉዳይ መፈጸምና ማስፈጸም፤
፲፭. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ ፩ እስከ ፲፬ የተዘረዘሩትን ተግባ ድሚያ እያጠና ተገቢውን ማድረግና አስፈላጊም ሆኖ ሲገኝ ጉዳ ለከታቸው ግለሰቦችና ድርጅቶች ጋር እየተነጋገረ ማስፈጸም፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## ስለ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሰበካ መንፈሳዊ ጉ

### አንቀጽ ፯

### የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባ አመሠራረትና አቋም

፩. አመሠራረት፤
ሀ) በአንድ ቤተ ክርስቲያን አጥቢያ ወይም ሰበካ ውስጥ የሚገኝ ምእመናንና የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች በዚህ ፡ መሠረት በአንድነት በመደራጀት የአንድ አጥቢያ ቤተ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤን ይመሠርታሉ፡፡
ለ) በዚህ አኳኋን የተመሠረተው የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ በዓ ጊዜ የሚሰበሰብ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ካህናትና በአንድነት የሚገኙበት ጠቅላላ መንፈሳዊ ጉባኤ ይኖረዋል፡፡
ሐ) የሰበካው ጠቅላላ መንፈሳዊ ጉባኤ በዚህ ቃለ ዓዋዲ በምዕ አንቀጽ ፭ እና ፮ የተዘረዘሩትን ዓላማና ተግባር እንዲችል በወር ሁለት ጊዜ እየተሰበሰበ የተጣለበትን ሥራ የሚያከናውን አንድ የአስተዳደር ጉባኤ ወይም የሥራ ኮሚቴ ይመርጣል፡፡
መ) በዚህ ቃለ ዓዋዲ ደንብ መሠረት በአጥቢያ ቤተ ክርስ መንፈሳዊ ጉባኤ ያልታወቀና ያልታቀፈ፣ በሀገረ ስብከ በጠቅላይ ቤተ ክህነት ያልተፈቀደ ምንም ዓይነት የምእመናን፣ የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች ማኅበር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስም መቋቋም አይችልም፡፡

፪. አቋም
በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ሥር፤

ሀ) የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ሊቀ መንበር የሆነበት አንድ ጠቅላላ መንፈሳዊ ጉባኤ (መላው የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ካህናትና ምእመናን ጠቅላላ ስብሰባ)፤
ለ) የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ሊቀ መንበር የሆነበት አንድ የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) ወይም የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳደር ጉባኤ፤
ሐ) የሰበካው መንፈሳዊ ጉባኤ ጽሕፈት ቤት (የቤተ ክርስቲያኑ ጽሕፈት ቤት)፤
መ) የሰበካው ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች የቤተ ክርስቲያኑ ልዩ ልዩ መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎቶች ናቸው፡፡

### አንቀጽ ፰

### ስለ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጠቅላላ መንፈሳዊ ጉባኤና የሥራ አፈጻጸም

፩. በሰበካው ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ወይም ጉዳዩ በሚመለከታቸው አካላት አማካይነት ለአጥቢያው ካህናትና ምእመናን ትምህርትና ቅስቀሳ ከተደረገ በኋላ አጠቃላይ ጥሪ ተደርጎ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡
፪. በቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ሊቀ መንበርነት የጠቅላላ መንፈሳዊ ጉባኤው አባላት የቤተ ክርስቲያንን ሕግና ሥርዓት በመከተል እርስ በእርሳቸው በመፈቃቀርና በመቻቻል ሥራውን ሁሉ በስምምነት ፥ በሰላምና በፀጥታ ይፈጽማሉ ፥ ያስፈጽማሉ ፤ ድምፅ የሚሰጥባቸው ጉዳዮችንም በድምፅ ብልጫ ይወስናሉ፡፡
፫. ድምፅ የመስጠት መብት ያላቸው አባላት፡-
ሀ) በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት የታወቁና በሰበካው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነዋሪ የሆኑ፤
ለ) በሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የተመዘገቡና መታወቂያ ካርድ ያላቸው፡፡
ሐ) ለቤተ ክርስቲያን የሚገባውን አስተዋጽኦ የከፈሉ፤
መ) ዕድሜያቸው ከ፲፰ ዓመት በላይ የሆኑ ምእመናንና ምእመናት ብቻ ናቸው፡፡
፬. የሰበካውን የምርጫ ሥነ ሥርዓት የሚያስፈጽም ከሰበካው ቤተ ክርስቲያን ልዩ ልዩ ቀበሌዎች ወይም ሠፈሮች የተውጣጡ ካህናት፣ ምእመናንና የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች የሚገኙበት ከአምስት ያላነሱ ከአሥራ

አምስት ያልበለጡ አባላት ያሉበት አስመራጭ ኮሚቴ መርጦ ይሠይማል፡፡ የኮሚቴው አባላት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ የተዘረዘሩት መስፈርቶች የሚያሟሉ፣ በመንፈሳዊነታቸው ፥ በግብረገብነታቸውና በአስተዋይነታቸው የታወቁ እንዲሁም በሕገ ቤተ ክርስቲያን የጸኑና በ ንስ ማንበብና መጻፍ የሚችሉ ይሆናሉ፡፡

፭. በዚህ ቃለ ዓዋዲ በአንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ ፫ መሠረት አዲስ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ምርጫ ከመካሄዱ ከአንድ ወር በፊት የቀየው የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ በሥራ ዘመኑ የፈጸማቸውንና ያስፈጸማቸውን ስለ ንብረት፣ ስለግምጃቤትና በባንክ ስለአለው ሒሳብና በዕቅድ ስለተያዙ ሥራዎች በአጠቃላይ የሥራና የፋይናንስ ሪፖርት ለጠቅላላው ጉባኤ እንዲቀርብ ይሆናል፡፡

፮. በዚህ ቃለ ዓዋዲ በአንቀጽ ፲ የተጠቀሱትን የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደ ጉባኤ (የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) አባላትን በአስመራጭ ኮሚቴው አማካይነት በእጩነት ከቀረቡት ተወዳዳሪዎች መካከል በድምፅ ብልጫ ይመርጣል፡፡

፯. በአስተዳደሩ ጉባኤ አቅራቢነት ጠቅላላው ጉባኤ በዚህ ቃለ ዓዋዲ በምዕራፍ አራት በአንቀጽ ፲፩ የተመለከቱትን የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የከፍ ሥራ ኃላፊዎችን (በቀዋሚ አገልግሎት ከሚሠየሙት በስተቀር) ይመርጣል፡፡

፰. በአስተዳደር ጉባኤ ተጠንቶ የሚቀርበውን ዓመታዊ የገንዘብ ድልድል (በጀት) መርምሮ ሲስማማበት እንዲፈቀድ ለመንበረ ጵጵስና ያስተላልፋል፡፡

፱. የሰበካውን ቤተ ክርስቲያን ገንዘብና ንብረት ጠቅላላ ገቢና ወጪ በበጀት ዓመቱ መጨረሻና በሌላም አስፈላጊ በሆነ ጊዜ በሒሳብ አጣሪ (ኦዲተር እንዲመረመር ያደርጋል፡፡

፲. ከአስተዳደር ጉባኤ የሚቀርበውን የሰበካውን ቤተ ክርስቲያን የገንዘብና ንብረት እንደዚሁም የሥራ ክንውን መግለጫና የኦዲት ሪፖርት ይሰማል፤ አከራካሪ የሆነ ጉዳይ ሲገጥምም በድምጽ ብልጫ ይወስናል፡፡

፲፩. የዚህ ጉባኤ ተጠሪነት ደረጃውን ጠብቆ ለወረዳ ቤተ ክህነት ይሆናል፡

## አንቀጽ ፬

## የአስመራጭ ኮሚቴው ተግባርና የሥራ አፈጻጸም

፩. አስመራጭ ኮሚቴው ዕጩዎችን የሚያጠናበት የተወሰነ ጊዜ ይኖረዋል

፪. ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልነት የሚወዳደሩ ዕጩዎችን አጣርቶና የምርጫውን አፈጻጸም አዘጋጅቶ ለአጥቢያው ካህናትና ምእመናን ጠቅ ጉባኤ ለምርጫ ያቀርባል፡፡

፫. መራጮቹም በዚህ ቃለ ዓዋዲ መሠረት በአንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ ፫ የተገለጸውን መስፈርት ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፡፡

፬. የምርጫው ድምፅ አሰጣጥ ከመጀመሩ አስቀድሞ አስመራጭ ኮሚቴው መራጮቹ የሚመርጧቸውን አባላት በትክክል እንዲያውቁና ብቁነታቸውንም እመዘዝነውና ተረድተው ለመምረጥ እንዲችሉ ትምህርትና ማብራሪያ እንዲሰጣቸው ያደርጋል፡፡

፭. የምርጫውም የድምፅ አሰጣጥ እንደ አካባቢውና እንደ አመችነቱ፡
   ሀ) በጽሑፍ ወይም
   ለ) በካርድ ወይም
   ሐ) እጅ በማውጣትና በማስቆጠር ሊሆን ይችላል፡፡

፮. የአስመራጭ ኮሚቴው ካቀረባቸው ዕጩዎች መካከል በጠቅላላው ጉባኤ ያልተደገፉ ቢኖሩ በጠቅላላው ጉባኤ ጠቋሚነት ሌሎች ዕጩዎች ቀርበው እንዲመረጡ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

፯. የድምፅ አሰጣጡ ሥነ ሥርዓት ከተፈጸመ በኋላ አስመራጭ ኮሚቴው ወዲያውኑ በጠቅላላው ጉባኤ ፊት ቆጥሮ የድምጽ ብልጫ ያገኙትን በቃለ ጉባኤ ከመዘገበና ከተፈራረመበት በኋላ ለጠቅላላው ጉባኤ ሰብሳቢ ለሆኑት ለቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ያቀርባል፡፡

፰. የቤተ ክርስቲያኒቱ አስተዳዳሪም በአስመራጭ ኮሚቴው የቀረበለትን የምርጫ ቃለ ጉባኤ ጸድቆ በሥራ ላይ እንዲውል ለወረዳው ቤተ ክህነት ያቀርባል፡፡

## አንቀጽ ፲

## የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) አባላት

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) የአባላት ዓይነትና ብዛት፤ የአባላት አመራረጥ፤ የተመራጮች አባላት መመዘኛ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ድንጋጌዎች መሠረት ይፈጸማል፡፡

፩. <u>የአባላት ዓይነትና ብዛት</u>

የሰበካው ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) ከዚህ ቀጥሎ እንደተመለከተው ከቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ጋር ከአምስት ያላነሱ ከዘጠኝ ያልበለጡ አባላት ይኖሩታል።

ሀ) የሰበካው ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ............ የጉባኤው ሊቀ መንበር
ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ (ሐ) እና (መ) ከተጠቀሱት ካህናትና ምእመናን አባላት መካከል የአስተዳደር ችሎታ ያለው ሆኖ በሕገ ቤተ ክርስቲያን የጸናና ግብረገብ የሆነ በዚሁ ጉባኤ የሚመረጥ ካህን ወይም ምእመን ዕድሜው ከ፴ ዓመት ያላነሰ ከ፸ ያልበለጠ፣ ............................................ የጉባኤው ም/ሊቀ
ሐ) በሰበካው ቤተ ክርስቲያን በግንባር ከሚያገለግሉት መደበኛ መካከል የሚመረጡ ከሁለት ያላነሱ ከአራት ያልበለጡ ............... ............................................................ የጉባኤው
መ) ከአንድ የሰንበት ት/ቤት ወጣት ጋር ከሰበካው ምእመናን የሚመረጡ ከሁለት ያላነሱ ከአራት ያልበለጡ ምእመናን ... ............................................................................ የጉባኤው
ሠ) በዚህ ቃለ ዓዋዲ በምዕራፍ አራት በአንቀጽ ፲፰ በንዑስ ን መሠረት ከመደበኛ አገልጋዮች መካከል የተመረጠው ካህን ቤተ ክርስቲያን ጸሐፊ ........................................ ጉባኤው

፪. <u>የአባላት አመራረጥ</u>

<u>ሀ) የካህናት ተመራጮች መመዘኛ</u>

ከካህናት ወገን የሚመረጡት አባላት፡-

(፩) ለአስተዳደር ሥራ ተገቢና ብቁ የሆኑ መደበኛ አገልጋይ
(፪) ሥጋዊ ጥቅምና የሥልጣን ሽሚያ ዘረኝነትና ጠባብ ብሔ አስተሳሰባቸውን ያዛባዋል ተብለው የማይጠረጠሩ፤
(፫) ከትዕቢት፣ከትንኮል፣ከአድማ፣ ከስካር፣ ከፍቅረ ንዋይ የራ ግብረገብነታቸውና ትሕትናቸው የተመሰከረላቸው፤
(፬) ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በጸሎት የሚተጉ ፣ ለስብከ ወንጌል የሚፋጠኑ፤
(፭) የገንዘብ ጉድለት ያልተገኘባቸው፣ በሌላም ወንጀል ተከሰ በጉባኤ ያልተወሰነባቸው ወይም በፍርድ ቤት ያልተፈረ ወይም በማናቸውም ሁኔታ መብታቸው በሕግ ያልተገደ ዕድሜያቸው ከ፲፰ ዓመት በላይ የሆኑ ይመረጣሉ።

ለ) <u>የምዕመናን ተመራጮች መመዘኛ፡-</u>

<u>ከምዕመናን ወገን የጾታ ልዩነት ሳይደረግ፡-</u>

(፩) በሥጋውና በደሙ የተወሰኑ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነ ዮች በአባልነት የተመዘገቡና አስተዋጽኦ የከፈሉ፤
(፪) ለቤተ ክርስቲያን አሳቢና ተቆርቋሪነታቸውን በተግባር ያ
(፫) ሥጋዊ ጥቅምና የሥልጣን ሽሚያ ዘረኝነትና ጠባብ ብሔ አስተሳሰባቸውን ያዛባዋል ተብለው የማይጠረጠሩ፤
(፬) ከትዕቢት፣ከተንኮል፣ከአድማ፣ከስካር፣ከፍቅረ ንዋይ የራቁ ብነታቸውና ትሕትናቸው የተመሰከረላቸው የገንዘብ ጉድ ተገኘባቸው በሌላም ወንጀል ተከሰው በጉባኤ ያልተወሰነ ወይም በፍርድ ቤት ያልተፈረደባቸው ወይም በማናቸውም መብታቸው በሕግ ያልተገደበባቸው፤
(፭) በአጥቢያው ነዋሪ የሆኑ ዕድሜያቸው ከ፲፰ ዓመት በላይ የሆኑ ምእመናንና ምእመናት ይመረጣሉ።

ሐ) <u>ከሰንበት ት/ቤት የሚመረጡት ቁጥራቸው ከምእመናን ወገን ሆኖ፡-</u>

(፩) በሰበካው የሰንበት ት/ቤት በአባልነት የተመዘገቡ፤
(፪) ዕድሜያቸው ከ፲፰ እስከ ፴ የሆኑ፤
(፫) ብቁ ችሎታ ያላቸውና በአስተዋይነታቸው የተመሰገኑ፤
(፬) በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት የጸኑ፤
(፭) ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መልካም ግንዛቤ ያላቸው ወጣቶች የጾታ ልዩነት ሳይደረግ ይመረጣሉ።

## አንቀጽ ፲፩

## ምርጫን ስለ ማጽደቅና ስለ ተመራጮች የአገልግሎት ዘመን

፩. ምርጫውን ስለ ማጽደቅና ስለ መሻር፦

ሀ) በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚፈጸመው የሰበካ ጉባኤ ምርጫ ሁሉ በወረዳው ቤተ ክህነት አቅራቢነት በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ይጸድቃል፡፡የምርጫው አፈጻጸም ትክክል ሆኖ ባያገኘው ሊቀ ጳጳሱ ምርጫውን በጉባኤ አይቶ ሊያሻሽለው ወይም ሊሽረው ይችላል፡፡

ለ) የሰበካ ጉባኤ አባላት ተመርጠው ሥራ ከጀመሩ በኋላ የገንዘብ መባከን ወይም ሌላ ችግር ቢፈጠር ሀገረ ስብከቱ በአስተዳደር ጉባኤ ሁኔታውን አጥንቶ የመሻር ሥልጣን አለው፡፡

፪. ለአባልነት የተመረጠው ካህን ወይም ምእመን በተመረጠበት አገልግሎት ላይ የሚቆየው ለሦስት ዓመት ነው፤ ይኸው አባል የሰጠው መልካም አገልግሎት እየታየ እንደገና ዕጩ ሆኖ በመቅረብ ሊመረጥ ይችላል፡፡ ስለሆነም ከሁለት ጊዜ በላይ በተከታታይ ሊመረጥ ስለማይችል አንዳንድ የምርጫ ጊዜ እያሳለፈ መመረጥ ይችላል፡፡

፫. በሥራ ላይ ያሉት የጉባኤው አባላት የሥራ ዘመን ከማለቁ ከአንድ ወር በፊት የአዲስ አባላት ምርጫ ይፈጸማል፤ ነገር ግን አዲስ የተመረጡት አባላት ሥራቸውን የሚጀምሩት በሥራ ላይ ያሉት አባላት የሥራ ዘመን ሲያበቃ ነው፡፡

፬. ስለ ተተኪ አባላት፤

አንድ አባል የሥራው ጊዜ ከማብቃቱ በፊት በሞት ወይም በዝውውር ምክንያት ወይም በአንቀጽ ፲ ንዑስ አንቀጽ ፪ ከ(ሀ) እስከ (ሐ) የተዘረዘሩትን የማያሟላ መሆኑ ሲታወቅ ወይም ለወረዳው አስተዳደር ጉባኤ በመመረጡ ወይም በሌላ ምክንያት ቦታው ክፍት የሆነ እንደሆነ ባለፈው ምርጫ ከተመረጡት አባላት ቀጥሎ ከፍተኛ ድምፅ ያገኘው አባል ሆኖ ቦታውን ይተካል፤ በዚህ ዓይነት የሚተካ አባል ከታጣ እንደገና ምእመናኑ ጠቅላላ መንፈሳዊ ጉባኤ ድምፅ ብልጫ ተመርጦ ክፍት ቦታ በአባልነት እንዲተካ ይደረጋል፡፡ ተተኪውም አባል የማ የዘመኑ ምርጫ እስኪፈጸም ድረስ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ ፲፪

## የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) ሥልጣንና ተግባር

በዚህ ቃለ ዓዋዲ በምዕራፍ ሁለት በአንቀጽ ፭ እና ፮ የ ዓላማና ተግባር እየፈጸመ በተጨማሪ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) የሚከተለው ተግባር ይኖረዋል፡፡

፩. የቤተ ክርስቲያን ሕግ በሚፈቅደው መሠረት የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ይጠብቃል፡፡

፪. ስለ ንዋየ ቅድሳት፥ ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት፥ ስለ ልዩ ልዩ ታ ቅርሶች አጠባበቅ እየመከረ ይወስናል፡፡

፫. በሰበካው ውስጥ ያሚነሱትን የሃይማኖትና የምሥጢራተ ቤተ ክ ጉዳይ የሚመለከት ልዩ የካህናት ጉባኤ ያቋቁማል፡፡

፬. በቃል ኪዳን፥ በተክሊልና በቁርባን በተጋቡት ባልና ሚስት መ ርቡትን ክሶች እና እንዲሁም ሥልጣነ ክህነትን እና ልዩ ልዩ ቤተ ክርስቲያንን የሚመለከቱ ጉዳዮች ሁሉ በተለይ ለዚሁ ተብ መው የካህናት ጉባኤ እንዲወሰን ያደርጋል፡፡ ጉዳዩ ከዚሁ ጉባኤ በላይ ሆኖ ከተገኘ ግን ደረጃውን ጠብቆ ወደ በላይ ያስተላልፋ

፭. ስለ ካህናት አስተዳደር ጉዳይ እያጠና ውሣኔ ይሰጣል፤ ይኸንን ለወረዳው ቤተ ክህነት ያስታውቃል፡፡

፮. ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጡትን ሕፃናትና ወጣቶች ከክፉ ነገ የመጠበቅ፥ የሚሰጣቸውም ትምህርት ሆነ የሚዘምሩት መዝሙ ዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ትውፊት መሠረት መሆኑን የማረጋገ ሥራቸውና ጠባያቸው ከክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ውጭ እንዳ የመከታተልና የመቆጣጠር ኃላፊነት አለበት፡፡

፯. ከዚህ ቃለ ዓዋዲ መሠረታዊ (መንፈሳዊ) ዓላማ ሳይወጣ በሰበካ ክርስቲያን ስም፦

ሀ) ውል መዋዋል

ለ) መክሰስና መከሰስ

ሐ) ሊሠራው በሚያስፈልገው መጠን የሚንቀሳቀስና የ ንብረት በውል ማከራየትና መከራየት

መ) ሥጦታዎችን መቀበልና የገቢ ምንጭ የሚገኝበትን የልማት ሥራ ማቋቋም

ሠ) አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም ለልማት ሥራ ገንዘብ መበደር ይችላል፡፡

፰. ከዚህ በላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በቋሚ ንብረቶችና ግምታቸው ከፍተኛ በሆኑ በማናቸውም ጉዳዮች ላይ ውል መዋዋል በአስፈለገ ጊዜ ከሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ፈቃድና መመሪያ እየተቀበለ ይሠራል፡፡

፱. ስለ ቤተ ክርስቲያኒቱ ሀብትና ንብረት አያያዝ እንዲሁም ስለውል አፈ ጻጸም ዝርዝር ጉዳይ ከበላይ አካል በሚወጣ ደንብና መመሪያ ይወሰናል፡፡

፲. በዚህ ቃለ ዓዋዲ በአንቀጽ ፶፮ ንዑስ አንቀጽ ፩ በተጠቀሰው መሠረት የሰበካው ምእመናን የሚከፍሉትን የአስተዋጽኦ ገንዘብ ልክ ያስታውቃል፤ ገቢ መሆኑንም ይቆጣጠራል፡፡

፲፩. ከሰበካው ቤተ ክርስቲያን ጠቅላላ ገቢ ውስጥ በዚህ ቃለ ዓዋዲ በአንቀጽ ፶፮ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላላ አስተዳደር ፥ ለትምህርትና ስብከተ ወንጌል ፥ ለልማትና በጐ አድራጎት እንደዚሁም በየሰበካው ለሚከናወኑት የንብረት ሥራ እቅዶችና ለልዩ ልዩ አገልግሎት የሚያስፈልገውን የገንዘብ አስተዋጽኦ ፳% (ሃያ ከመቶ) ለመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት በወቅቱ ገቢ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

፲፪. በማዕከል ደረጃ ተፈቅዶ አዲስ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ፥ ትምህርት ቤት ፥ ክሊኒክና የመሳሰሉት በሚሠሩበት ጊዜም ቢሆን ከግለሰብ ፥ ከልዩ ልዩ ድርጅቶችና ከበጐ አድራጊዎች በርዳታ ከሚገኘው በስተቀር ከልማትም ሆነ ከማናቸውም ገቢ ላይ ፳% (ሃያ ከመቶ) እንዲከፈል ያደርጋል፡፡

፲፫. ማናቸውንም የቤተ ክርስቲያኑን ገቢ ገንዘብ በሰበካው ቤተ ክርስቲያን ስም ባንክ ያስቀምጣል፡፡

፲፬. በዚህ ቃለ ዓዋዲ በአንቀጽ ፶፮ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የቤተ ክርስቲያኑን ዓመታዊ የገንዘብ ድልድል (በጀት) መርምሮ የሰበካው ካህናትና ምእመናን ጠቅላላ መንፈሳዊ ጉባኤ አውቆት ከተስማማበት በኋላ እንዲፈቀድ ደረጃውን ጠብቆ ለመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት መንፈሳዊ ጉባኤ ጽ/ቤት እንዲቀርብ ያደርጋል፤ የመንበረ ጵጵስና መንፈሳዊ ጉባኤም የቀረበውን በጀት መርምሮ ሲስማማበትና በጀቱን አጽድቆ መልሶ ሲልክለት በተግባር እንዲውል ያደርጋል፡፡

፲፭. ከቤተ ክርስቲያኑ ጽ/ቤት በተወሰነው ጊዜ የሚቀርበውን የሥራ መግ ለጫና የሰበካው ተቆጣጣሪ የሚያቀርበውን የሒሳብ ምርመራ ውጤት ሰምቶ ውሳኔ ያሳልፋል፡፡

፲፮. የሰበካው ቁጥጥር ክፍል ሒሳቡን ለመመርመርና ለመቆጣጠር ከአቅሙ በላይ መሆኑ ሲታወቅ ከሀገረ ስብከቱ ፥ ከዚያም በላይ ሆኖ ሲገኝ ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ተቆጣጣሪ እንዲላክለት በመጠየቅ ሊያስመረምር ይችላል፡፡

፲፯. የቤተ ክርስቲያኑን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ጽ/ቤትና የሥራ ክፍሎችን ያቋቁማል፡፡

፲፰. በሰበካው ውስጥ ሕንፃ ለመሥራት አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ለታቀደ ከሀገረ ስብከቱ ፈቃድ በማግኘትና መመሪያ በመቀበል የሕንፃ ኮሚቴ ያቋቁማል፡፡ የዚህን ኮሚቴ አባላትም በጠቅላላው ጉባአ ርጣል፡፡

፲፱. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፲፫ ከተጠቀሰው ሌላ ለሕንፃው ሥ ስብከቱ ፈቃድ የተለየ የባንክ ሒሳብ ቁጥር በቤተ ክርስቲያኑ ፣ እንዲከፈት ያደርጋል፡፡

፳. ከባንክ ገንዘብ ወጪ በሚደረግበት ጊዜ፦

ሀ) መደበኛው የሰበካ ጉባኤ ወጪ ሒሳብ ከሆነ በቤተ አስተዳዳሪና በሰበካው ም/ሊቀ መንበር በሁለቱ ጣምራ

ለ) የሕንፃው ሥራ ወጪ ከሆነ በአስተዳዳሪውና በሕንፃ አ ዋና ሊቀ መንበር ወይም የኮሚቴው ዋና ሊቀ መንበር በኮሚቴው ም/ሊቀ መንበር ጣምራ ፊርማ በወጪ ቅ ላይ እየተፈረመ ገንዘቡ እንዲወጣና በሥራ ላይ ያደርጋል፡፡

፳፩. የዚህን ቃለ ዓዋዲ መሠረታዊ ሐሳብ ሳይለቅ ለሰበካው ቤተ ] የሚያስፈልገውን የውስጥ መተዳደሪያ ደንብና መመሪያ እንዲ የሥራ እቅድ አዘጋጅቶ የአጥቢያው ካህናትና ምእመናን ጠቅ አውቆት ሲስማማበት እንዲፈቀድ በወረዳው ቤተ ክህነት በኩ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ እንዲቀርብ ያደርጋል፡፡

፳፪. በተፈቀደው የውስጥ መተዳደሪያ ደንብና መመሪያ እንዲሁም መሠረት ለልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች ዝርዝር የሥራ መርሐ ግ ያዘጋጃል፤ አፈጻጸሙንም ይቆጣጠራል፡፡

፳፫. በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ውስጥ የተቋቋሙት የሥራ የሚወስኑትን ልዩ ልዩ ጉዳዮች እየመረመረ ያጸድቃል ፤ ያሻ ይሽራል፤

፳፬. በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን የሚገኙት አባላት በግላቸው በሚ ጥፋት አስተዳደር ነክ የሆነውን አይቶና መርምሮ ውሳኔ ይሰጣ ዲሲፒሊን ነክ የሆኑትን ጉዳዮች ግን በሕግና በሥነ ሥርዓት ] እንዲታይ ያደርጋል፡፡

፳፭. በሕግና ሥነ ሥርዓት ኮሚቴ የተወሰነውን የማየት ሥልጣን ፣
፳፮. ከመንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ አባላት መካከል ለወረዳው ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ አንድ ካህን፣አንድ ምእመንና አንድ የሰንበት ወጣት መርጦ ይልካል::
፳፯. ከአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ሰበካ አስተዳደር ጉባኤ(ሥራ አስ ኮሚቴ) መካከል ለወረዳው አስተዳደር ጉባኤ አባል እንዲሆኑ ጣቸውና በሌላም ምክንያት የአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን አስተ ጉባኤ አባላት ቁጥር ከአምስት ያነሰ እንደሆነ ከአስተዳዳሪው በምትካቸው በአንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ ፬ በተመለከተው መ ሌሎች ተመሳሳይ አባላትን ይተካል::
፳፰. በዚህ ቃለ ዓዋዲ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ ፩(ለ) መሠረት በ

ወር በሚደረገው ስብሰባና የሰበካ አስተዳደር ጉባኤው የሥራ ጊዜውን ከመፈጸሙ ከአንድ ወር በፊት ስለአከናወናቸው ሥራዎችና የገንዘብ ወጪዎች በማስመልከት ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባኤው ያቀርባል::
፳፱. የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) ተጠሪነቱ ለአጥቢያው ካህናትና ምእመናን ጠቅላላ ጉባኤ ይሆናል::

## አንቀጽ ፲፫

## የሰበካው ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ (የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ሊቀ መንበር) ሥልጣንና ተግባር

በዚህ ቃለ ዓዋዲ በአንቀጽ ፭ እና ፮ የተመለከተውን ዓላማና ተግባር ለመፈጸም አስተዳዳሪው(ሊቀ መንበሩ) የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል::

፩. የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ የሰበካው ቤተ ክርስቲያን ዋና ሥራ አስፈጻሚ (ሥራ አስኪያጅ) በመሆን በዚህ ቃለ ዓዋዲና ይህን ቃለ ዓዋዲ ተከትሎ በሚወጣው የውስጥ ደንብ መሠረት ስለ ሰበካው ካህናትና ምእመናን ጠቅላላ መንፈሳዊ ጉባኤና ስለ አስተዳደሩ ጉባኤ የሥራ አፈጻጸም በጠቅላላው በሰበካው ቤተ ክርስቲያን ላለው አስተዳደር ኃላፊና ተጠሪ ነው::
፪. ስለ ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች አስተዳደር ከቅዱስ ሲኖዶስ በወጣውና በሚወጣው ደንብ መሠረት የሰበካውን ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ይመራል::
፫. የአጥቢያው ሰበካ ጉባኤ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ምርጫ ከመከናወኑ በፊት ለአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ጠቅላላ ካህናትና ምእመናን የቅስቀሳ ትምህርት ይሰጣል፤ እንዲሰጥም ያደርጋል::
፬. በሰበካው ውስጥ የስብከተ ወንጌል፣ የትምህርት፣ የካህናት አገልግሎት፣ የሰንበት ት/ቤት፣ የምግባረ ሠናይና የማኅበራዊ ኑሮ አገልግሎቶች ባሉት ደንቦችና ሥርዓቶች መሠረት እንዲደራጁና በትክክል ሥራ ላይ ውለው እንዲስፋፉ ተገቢውን ጥረትና ጥብቅ ቁጥጥር ያደርጋል፤ የልዩ ልዩ ክፍል ሥራዎችንም ያስተባብራል፤ ይቆጣጠራል::
፭. የቤተ ክርስቲያኑ አገልጋዮች ካህናትና ምእመናን መታወቂያ ያላቸው መሆናቸውንና በሰበካው ውስጥ ያሉት ምእመናን ሁሉ መመዝገባቸውን የጥምቀት፣ የጋብቻና የሙታን መዝገብት እየተሠራባቸው መሆኑን ያረጋግጣል::
፮. የሰበካውን ምእመናንና የምእመናኑንም ልጆች ከኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ምግባርና ሃይማኖት እንዳይወጡ ይጠብቃል፥ ያስጠብቃል፤ በጠቅላላው ካህናትን ይልቁንም የንሥሐ አባቶችን በጥበቃው ተግባር እንዲጠናከሩ መመሪያ ይሰጣል፥ ይቆጣጠራል::
፯. የቤተ ክርስቲያኑ ገቢ በትክክል እንዲሰበሰብ ገንዘቡና ማናቸውም የ ቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ሀብትና ንብረት እንዲጠበቅና በአስተዳደሩ ጉ እየታየ በሚወሰነው መሠረት በተገቢው ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላ
፰. ከበላይ በተፈቀደው ዓመታዊ የገንዘብ ድልድል (በጀት) መሠረት ማ ውንም ወጪ በማዘዝ እንዲሠራበት ያደርጋል::
፱. በዚህ ቃለ ዓዋዲ አንቀጽ ፲፪ በንዑስ አንቀጽ ፯ እስከ ፱ የተደነገገወ ጠብቆ የውሉ ረቂቅ በአስተዳደሩ ጉባኤ ሲጸድቅ ከም/ሊቀ መንበሩ ጋ ሆኖ በቤተ ክርስቲያኑ ስም ውል ይዋዋላል፤ ይፈርማል::
፲. የአስተዳደሩ ጉባኤ እንዲሰበሰብ ጥሪ ያስተላልፋል፤ በጉባኤ በተሰጠ ውሣኔ መሠረት እንዲሠራበት እያደረገ አፈጻጸሙን ይቆጣጠራል::
፲፩. የሰበካው መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ አባላትን፣ የዋና ጸሐፊውንና ልዩ ክፍል ኃላፊዎችን ምርጫ እንዲጸድቅለት ለወረዳው ቤተ ክህነት ያቀርባል::

፲፪. በሰበካው መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ስም አስተዳዳሪው ስለ ሰበካወ ካህናትና ምእመናን ሁኔታ፣ ስለ ቤተ ክርስቲያኑ አገልጋዮች፣ስለ ገ ብና ንብረት እንዲሁም ስለ ልዩ ልዩ ክፍሎች የሥራ ክንውን መግ ለሰበካው ቤተ ክርስቲያን ካህናትና ምእመናን ጠቅላላ መንፈሳዊ ጉ በዓመት ሁለት ጊዜ ያቀርባል፤ የጠቅላላ ጉባኤውንም ውሳኔ ለወረዳ ቤተ ክህነት ያስተላልፋል::

፲፫. ከዚህ ሌላ በዚህ ቃለ ዓዋዲ መሠረት በሚሰጠው መመሪያ የሚወሰ ለትን ተግባር ሁሉ ይፈጽማል፤ ያስፈጽማል::

፲፬. አስተዳዳሪው ቅጥርን፣ ደመወዝ ጭማሪን፣ ዕድገትንና ዝውውርን የ ለከቱ ጉዳዮችን ሁሉ የሰበካው ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሳይነጋገርበት ሳይወስን እንዲሁም የበላይ አካል ሳያውቀውና ሳይፈቅድ ብቻውን መፈጸም አይችልም::

## አንቀጽ ፲፬

## ስለ አጥቢያው ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ም/ሊቀ መንበር

፩. የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ በሌለ ጊዜ ም/ሊቀ መንበሩ የአስተዳዳሪ ተግባር ይፈጽማል::

፪. ም/ሊቀ መንበሩ ሥልጣነ ክህነት የሌለው ከሆነ ምሥጢራተ ቤተ ክ ቲያንን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ማየት አይችልም::

፫. ም/ሊቀ መንበሩ ተጠሪነቱ ለቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ነው::

## አንቀጽ ፲፭

## ስለ ገዳማት አስተዳደርና ሥርዓተ ምንኩስና

፩. <u>የገዳማት አስተዳደር ፣</u>

ሀ) የአንድነት ገዳማት የሚተዳደሩበት ራሱን የቻለ የገዳም ደንብና መመሪያ ይኖረዋል::

ለ) ሥርዓተ ገዳም በሚፈቅደው መሠረት በየገዳማቱ ውስጥ ጽ/ቤቶችና ልዩ ልዩ የአመራር አካላት ይቋቋማሉ::

ሐ) በገዳሙ አስተዳደር መሠረት የጸም ጸሎት ሥርዓት እንደተጠበቀ ሆኖ መነኮሳት የሚማሩበት ቦታና በልዩ ልዩ አገልግሎት የሚሠማሩበት የሥራ መስኮች ይዘጋጃሉ::

መ) መነኮሳይያትም በተወሰነላቸው የገዳም ክልል ጸንተው በሥርዓተ ምንኩስና መሠረት ራሳቸውንና ሌሎችንም እየረዱ እንዲኖሩና እንዲሠሩ ይደረጋል::

ሠ) ገዳማት የየራሳቸው የተከበረ የቦታ ክልል እንዲኖራቸው ሆኖ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው በስተቀር የገዳማት ክልሎች የሕዝብ መሥፈሪያ አይሆኑም::

ረ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ ፫ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በአንድነት ገዳማት ዙሪያ የሚኖሩ ምእመናን በሰበካ ጉባኤ ቢደራጁም ባይደራጁም በዓይነት ወይም በጥሬ ገንዘብ አስተዋጽኦ እንዲከፍሉ ይደረጋል::

ሰ) ሰበካ ጉባኤ በተቋቋማባቸው ገዳማት ምእመናኑ ከከፈሉት አስተዋ ጽኦና ከልዩ ልዩ ገቢያቸው ላይ ከመቶ ሃያ ፳% ለሀገረ ስብከት ይከፍላሉ::

ሸ) በገዳማት የሚኖሩ መነኮሳትም ሆኑ መነኮሳይያት እንዲሁም በገዳማት ዙሪያ የሚኖሩ ምእመናን በገዳሙ አማካይነት በሰበካ ጉባኤ ቅጽ ይመዘገባሉ::

ቀ) ማዕረገ ምንኩስና የሚሰጠው በገዳሙ አስተዳደር ቁጥጥር ውስጥ በአመክሮ ለሦስት ዓመት ለቆዩና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት መመዘኛውን ላሟሉት ብቻ ይሆናል::

በ) በሊቀ ጳጳስ ታውቆና ተፈቅዶ ካልሆነ በቀር ማዕረገ ምንኩስና ከገዳም ውጭ አይሰጥም::

፪. <u>የገዳም አስተዳዳሪ</u>

ሀ) የገዳም አስተዳዳሪ በማኅበረ መነኮሳትና መነኮሳይያት የሚገለገለውን የአንድነት ገዳም ከቅዱስ ሲኖዶስ በሚሰጠው መመሪያና ውሳኔ መሠረት ያስተዳድራል::

ለ) ከገዳሙ ውስጥ በግብረ ገብነታቸው ፣ በትምህር‍ በጸሎታቸው ትሩፋት ይሠራሉ ተብለው የሚታመ መነኮሳት ተመርጠው ሲቀርቡ በሊቀ ምርፋቅነት በሊቀ ትንትና በዕጓል መጋቢነት እየሠየመ እንዲሠሩ ያደርጋል::

ሐ) የገዳሙ መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት የሚሰፋ፡ መነኮሳትና መነኮሳይያት በተግባረ ዕድ ሙያ የሚሠለጠ ራሳቸውንም ሆነ ገዳሙን የሚረዱበትን ልማት ያቋቁማል፡፡

መ) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ ፫ የተገለጸውን መ የሚያሟሉ መሆናቸው የተረጋገጠላቸውና ለምንኩስና ለመሆናቸው ከገዳሙ አስተዳደር የተወሰነላቸው ሰዎች በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ወይም በዚሁ ገዳም ውስጥ ም እንዲቀበሉ ያደርጋል፡፡

ሠ) የምንኩስና ማዕረግ ለተቀበሉ መነኮሳት ወይም መነ የምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው ያደርጋል፡፡

ረ) ያለበቂ ምክንያትና ያለገዳሙ ፈቃድ ከገዳሙ ክልል የሚወጡትንና የሚገቡትን መነኮሳት በጥብቅ ይቆጣጠራል ቅጣትም ይሰጣል፡፡

## ፫. <u>የምንኩስና መመዘኛ ፣</u>

### ሀ) <u>ሥርዓተ ምንኩስናን የሚቀበሉ ምእመናንና ምእመናት</u>

(፩) በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትና ሥነ ምግባር የጸኑ ናቸው የተመሰከረላቸው፤

(፪) የምንኩስናን ዓላማና ተግባር በትክክል የተረዱና ይህን ለመፈጸም ቁርጥ ሐሳብ ያላቸው፤

(፫) ከምንኩስና በፊት በድንግልና ወይም በጋብቻ ለመኖራ የታወቁ፤

(፬) ልዩ ችግርና በቂ ምክንያት ከሌለ በቀር ዕድሜያቸው ዓመት በላይ የሆኑ፤

(፭) ጤናማ አእምሮ ያላቸው፣ ትዕግሥተኛና አርቆ አስተዋ መሆናቸው የተረጋገጠላቸው፣

(፮) በገዳም ውስጥ ሦስት ዓመት በአመክሮ መቆየት የሚኘ ረገ ምንኩስና ይቀበላሉ፡፡

(፯) የሦስት ዓመቱ አመክሮ ዕድሜያቸው ከ፴ ዓመት በ የሆኑትን ምእመናንና ምእመናት አይመለከትም፡፡

### ለ) <u>በክህነት ሥራ ለማገልገል ማዕረገ ምንኩስናን ለሚቀበሉ የበ ክርስቲያን አገልጋዮች</u>

(፩) በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ (ሀ) ከ(፩) እስከ (፯ ረዘረውን ማሟላታቸው በማስረጃ የተረጋገጠላቸው፤

(፪) መጻሕፍተ መነኮሳትን የሚያውቁና ሥርዓተ ገዳምን የሚጠ ብቁ፤

(፫) የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ያላቸውና ቅዱሳት መጻሕፍትን የተማሩ፤

(፬) በአርአያነታቸውም ሆነ በትምህርታቸው የታወቁና ችሎታ ያላቸው ማዕረገ ምንኩስናና ክህነት ይሰጣቸዋል፡፡

## ፬. <u>ከምንኩስና በኋላ</u>

ሀ) ሥርዓተ ምንኩስና ሲቀበሉ በገቡት ቃል ኪዳን መሠረት እስከ ዕድሜያቸው መጨረሻ ድረስ በምንኩስናቸው መጽናት ይኖርባቸዋል፡፡

ለ) በመነኮሱበት ገዳም እንደየስጦታቸውና እንደየችሎታቸው መጠን አገልግሎት መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ሐ) በቀዋሚነት ከሚኖሩበትና ከሚያገለግሉበት ገዳም ያለበቂ ምክንያትና ያለገዳሙ ፈቃድ ወደ ወጭ መውጣት የተከለከለ ነው፡፡

መ) በልዩ ልዩ ምክንያት ተፈቅዶላቸው ከገዳም ውጭ የሚኖሩ መነኮሳትና መነኮሳይያት ሥርዓተ ምንኩስናቸውን ጠብቀው ከክፉ ነገር ርቀው በመልካም ሥነ ምግባር ለአካባቢያቸው ሕዝበ ክርስቲያን አርአያ መሆን አለባቸው፡፡

ሠ) በምንኩስና ሥርዓት ለሚኖሩ መነኮሳትና መነኮሳይያት ከማይስማማ የሥራ ዓይነትና መገኘት ከማይገባቸው ቦታ መከልከል ግዴታቸው ነው፡፡ የምንኩስና ምልክታቸው የሆነው ቆባቸው ከራሳቸው ላይ እንዳይለይ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

ረ) በገጠርም ሆነ በከተማ በሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት በልዩ ልዩ አገልግሎት የተመደቡ መነኮሳት በአኗኗራቸውና በአነጋገራቸው ለካህናትና ምእመናን የመልካም ሥነ ምግባር አብነት መሆን ይገባቸዋል፡፡

ሰ) ሳይበቁ በቅቻለሁ ብሎ ከመመጻደቅና ከውዳሴ ከንቱ ርቆ ለመነ ኮሳት የሚስማማውን ትሕትናና ትዕግሥትን መያዝ አለባቸው፡፡

ሸ) ከመነኮሳት መካከል ተመርጠውና ችሎታቸው ተመዝኖ ሥልጣን ባለው የቤተ ክርስቲያኒቱ አካል ካልተፈቀደ በስተቀር ማስተማር አይገባቸውም፡፡

# ምዕራፍ አራት

## ስለ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ጽ/ቤትና የሥራ ክፍሎች

### አንቀጽ ፲፮

### የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ጽ/ቤትና የሥ ክፍሎች መቋቋም፣ የሥራ ኃላፊዎች ምርጫና የአገልግሎት ዘ

፩. የሰበካው መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) በዚ ዓዋዲ አንቀጽ ፰ እና ፯ የተገለጸውን ዓላማና ተግባር ለመፈጸም እ ችል አንድ ጽ/ቤትና ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ልዩ ልዩ የሥራ ክ ያቋቁማል።

ሀ) የስብከተ ወንጌል ክፍል
ለ) የመንፈሳዊ ትምህርት ክፍል
ሐ) የካህናት አገልግሎት ክፍል
መ) የሰንበት ት/ቤት ክፍል
ሠ) የእቅድና ልማት ክፍል
ረ) የምግባረ ሠናይ(በጐ አድራጐት) ክፍል
ሰ) የሕግና ሥነ ሥርዓት ክፍል
ሸ) የንብረት፣ የዕቃ ግምጃ ( የታሪካዊ ቅርስ ክፍል
ቀ) የሒሳብ ክፍል
በ) የገንዘብ ቤት
ተ) የቁጥጥር ክፍል
ቸ) የሕንፃ ሥራ፣ እድሳትና ክፍል
ኀ) የስታቲስቲክስ ክፍል

፪. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ ፩ ከ(ሀ) እስከ (ኀ) የተዘረዘሩት የሥ ክፍሎች የሥራ ዓይነትና ጠባይ እንደ ተጠበቀ ሆኖ ተመሳሳይ የሆነ የማይቃረነውን ክፍል ሁለትና ሦስቱን አንድነት በማደራረብ በአንዳን የሥራ ኃላፊዎች ማሠራት ይቻላል፤ እንደሁኔታውም እየታዩ ኮሚቴ ለሚያስፈልጋቸው የሥራ ክፍሎች ኮሚቴ ማቋቋም ይቻላል።
፫. በሰበካው ጉባኤ ጽ/ቤት አንድ ጸሐፊና በቋሚነት የሚመደቡ የየክፍ ኃላፊዎች ይኖራሉ።
፬. ለዋና ጸሐፊነትም ሆነ ለክፍል ኃላፊነት በግብረገብነታቸው በችሎታ በሥራ ልምዳቸው የተመሰከረላቸው ካህናት የወረዳው ቤተ ክህነት ; በተገኘበትና የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ሰብሳቢ በሆነበት በካህናት ተመርጠው ይመደባሉ።
፭. በገንዘብ ያዥነትና በንብረት ኃላፊነት የሚመደቡት ሠራተኞች በቂ ሀብትና ንብረት ያለው ተያዥ ማቅረብ ግዴታቸው ይሆናል።
፮. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ ፩ ከ(ሀ) እስከ (ኀ) ለተዘረዘሩት ክፍ ኃላፊዎችን በቀዋሚነት መመደብ በማይቻልበት አካባቢና ጊዜ በግብ ገብነታቸው፤ በችሎታቸውና በሥራ ልምዳቸው የተመሰከረላቸው እጩዎች በአስተዳደሩ ጉባኤ አማካይነት ቀርበው በጠቅላላው ጉባኤ ይመረጣሉ።
፯. በደመወዝ ከሚቀጠሩት ቀዋሚ አገልጋዮች ሌላ በበጐ ፈቃድ እንዲያ ገለግሉ የሚመረጡት የየክፍሉ ኃላፊዎች የአገልግሎት ዘመናቸው በዚህ ቃለ ዓዋዲ በአንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ ፪ ስለ ሰበካው መንፈሳዊ አስተዳ ደር ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) አባላት የአገልግሎት ዘመን በተመለ ከተው መሠረት ይፈጸማል፤ ስለሆነም የየክፍሉ የሥራ ኃላፊዎች ምርጫ የሚደረገው የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) አባላት ከተመረጡ በኋላ ነው።
፰. በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የተቋቋሙትና የሚቋቋሙት የሥራ ክፍሎች ተጠሪነታቸው ለቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ይሆናል።

### አንቀጽ ፲፯

### የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ዋና ጸሐፊ ሥልጣንና ተግባር

፩. የሰበካው መንፈሳዊ ጉባኤ ዋና ጸሐፊ ተጠሪነቱ ለቤተ ክርስቲያኑ አስተ ዳዳሪ ሆኖ በሰበካው ቤተ ክርስቲያን ጽ/ቤት ውስጥ የሚከናወኑትን ጠቅላላ የጽሕፈት፣ የሒሳብና የንብረት አጠባበቅ ሥራዎችን እንደዚሁም የልዩ ልዩ ክፍሎችን የሥራ እርምጃ በቅርቡ እየተከታተለ በመቆጣጠር ይሠራል ያሠራል።
፪. የሰበካውን ካህናትና ምእመናን እየመዘገበ የአባልነት መታወቂያ ካርድ ይሰጣል።

፫. ሕፃንም ሆነ አዋቂ ክርስትና ሲነሣ የክርስትና ስሙ ፥ የወላጅ አባትና እናት ስም፥ የክርስትና አባት ወይም እናት ስም፥ የትውልድ ቦታ(ሀገር) እና የተወለደበት ቀንና ዓመተ ምሕረት በመዝገበ ጥምቀት እንዲጻፍ፥ እንዲሁም ጋብቻቸውን በቤተ ክርስቲያን የፈጸሙ ተጋቢዎች እንዲመዘ ገቡና የምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው ያደርጋል፡፡

፬. ከእያንዳንዱ የሰበካው አባል ሊከፈል የሚገባው አስተዋጽኦ በወቅቱ ገቢ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

፭. መዝገብ ቤቱን ያደራጃል፤ ሥራውም በሥርዓት እንዲመራና ልዩ ልዩ ጽሑፎች፣መዛግብትና ማኅደረ ጉዳዮች ሁሉ እንዲጠበቁ ያደርጋል፤ የመዝገብ ቤት ሠራተኛ በሌለበት ጊዜም ደርቦ ይሠራል፡፡ እንዲሁም በሕይወት ያሉትንና በሞት የተለዩትን የምእመናን ስም እየመዘገበ በክብር እንዲቀመጥ ያደርጋል፡፡

፮. የጽ/ቤቱን ማኅተም በኃላፊነት ይዞ በአስተዳዳሪው ወይም እርሱ በሌለ ጊዜ ም/ሊቀ መንበሩ የሚፈርምባቸውን ደብዳቤዎች ወይም ም/ሊቀ መንበሩ በሌለ ጊዜ ታውቆና ተፈቅዶ ሲሠራበት የቆየውን የተለመደ ተግባር እሱ እየፈረመና እያተመ ለባለ አድራሻው እንዲላክ ያደርጋል፤

ደራሽ ደብዳቤዎችንም ይቀበላል፡፡

፯. ስለ ቤተ ክርስቲያኑ የሥራ አፈጻጸምና የሒሳብ ይዞታ መግለ ጭው ዓመት ከሚፈቀደው ዓመታዊ የገንዘብ ድልድል (በጀት) አዘጋጅቶ በአስተዳዳሪው አማካይነት ለአስተዳደሩ ጉባኤ ያቀርባ

፰. የአስተዳደሩ ጉባኤ ጸሐፊ ሆኖ በስብሰባው ላይ በመገኘት ጉባኤ ጋገረባቸውን ዝርዝር ነገሮችና ውሳኔ የተሰጠበትን ቃለ ጉባኤ አባላቱ እንዲፈርሙበት ያደርጋል፤ እርሱም በጸሐፊነቱ ይፈር

፱. በቤተ ክርስቲያኑ ጠቅላላ ሰበካ ውስጥ ሃይማኖትን፣ የቤተ ክር መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎትን በሚመለከት ጉዳይ ላይ ስ አንዳንድ ሁኔታዎች አስተዳዳሪውንና የአስተዳደሩን ጉባኤ እያ እንዲጠና ያደርጋል፡፡

፲. የቤተ ክርስቲያኑ ካህናትና ልዩ ልዩ ሠራተኞች በየተግባራቸው መሥራታቸውን በመቆጣጠር ሁኔታውን በየጊዜው ለአስተዳዳሪ ረብ ተገቢውን ይፈጽማል፥ ያስፈጽማል፡፡

፲፩. የሰበካውን ቤተ ክርስቲያን አባላትና አገልጋዮች ሁኔታ፣ የገን ንብረት መግለጫ፣ የጽ/ቤቱንና ከሰበካው ልዩ ልዩ የሥራ ክፍ የሚቀርብለትን የሥራ ክንውን እንዲሁም እስታቲስቲካዊ መረ በማጠቃለል በየሦስት ወሩ ለአስተዳደሩ ጉባኤ ሪፖርት ያቀር

፲፪. ከአስተዳዳሪው የሚታዘዘውን ማንኛውንም የቤተ ክርስቲያን ይፈጽማል፤ ያስፈጽማል፡፡

፲፫.የሰው እጥረት ባለበት ቦታም፤ የአስተዳደር ጉባኤው ሲወስን የ ኃላፊውን ሥራና ኃላፊነት ደርቦ ይሠራል፡፡

## አንቀጽ ፲፰

## የስብከተ ወንጌል ክፍል ሥራና ኃላፊነት

፩. የስብከተ ወንጌል ክፍል የዕለትና የዘወትር መርሐ ግብር በማ በዕለተ ሰንበትና በዓበይት በዓላት ለሕዝበ ክርስቲያኑ ትምህር ያደርጋል፡፡

፪. አመቺ በሆነ ጊዜና ቦታ ምእመናንን በመሰብሰብ የቅዱሳት መ ትምህርት ያስጠናል፡፡

፫. የቅዳሴ ሥነ ሥርዓት በሚፈጸምበት ጊዜ ስብከተ ወንጌል መስ ይከታተላል፡፡

፬. ኅብረተሰቡ በሚረዳውና በሚያውቀው ቋንቋ ትምህርተ ወንጌል የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮች ምእመናን እንዲበዙ ጉባኤም እንዲመዘገቡ በማድረግ ሐዋርያዊ ተልዕኮውን ይፈጽማ ያስፈጽማል፡፡

፭. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ቤተ ጡትን ጋዜጦችና መጽሔቶች እንዲሁም ልዩ ልዩ እትሞችን እየተቀበለ ለምእመናን በወቅቱ የማድረስ ኃላፊነት አለበት፡፡

፮. ከኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ውጭ የሆኑ መጻሕፍትና ልዩ ልዩ እትሞች ለምእመናን እንዳይሠራጩ ይቆጣጠራል፡፡

፯. ሳይማሩ ተምረናል ሳይላኩ ተልከናል በማለት ያለ ፈቃድ እንሰብካለን እናስተምራለን የሚሉትን ሕገ ወጥ ግለሰቦችን የመቆጣጠር ኃላፊነት አለው፡፡

## አንቀጽ ፲፱

## የመንፈሳዊ ትምህርት ክፍል ሥራና ኃላፊነት

፩. እያንዳንዱ የሰበካ ቤተ ክርስቲያን አቅሙ በሚፈቅድለትና ከቅዱስ ሲኖዶስ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት በቤተ ክርስቲያን አካባቢ መንፈሳዊ ት/ቤት እንዲቋቋም ያደርጋል፡፡

፪. በዚህ ት/ቤት፦
   ሀ) የንባብ፣ የጽሕፈት፣ የስሌትና የቋንቋ፤
   ለ) የጸዋትወ ዜማ፣ የአቋቋምና የቅዳሴ፤
   ሐ) የግዕዝ (ቅኔ)፤
   መ) የትርጓሜ መጻሕፍት (ትምህርተ ሃይማኖት)፤
   ሠ) የቤተ ክርስቲያን ታሪክ፤
   ረ) የኪነ ጥበባት ፣ የተግባረ ዕድና ልዩ ልዩ የሙያ ትምህርቶች እንዲሰጡ ያደርጋል፡፡

፫. የሰበካውን ሕፃናት እየሰበሰበ ፊደል ከማስቆጠር ንባብ ከማስተማር ጋር መሠረተ ሃይማኖትን እንዲያውቁና ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር እንዲኖራቸው ማድረግ ተቀዳሚ ተግባሩ ነው፡፡

፬. ስለ ትምህርቱም ከቅዱስ ሲኖዶስ በሚወጣው ደንብና ሥርዓተ ትምህርት መሠረት መርሐ ግብር በማዘጋጀት የትምህርቱን ይዞታና አመራር ይከታተላል፡፡

፭. በሕፃናት ተማሪዎች ላይ የሚፈጸመው ቅጣት የመንፈስና የአካል ጉዳት በሚያደርስ ጭካኔ በተሞላበት መንገድ እንዳይሆን ይቆጣጠራል፡፡

፮. የትምህርት መስጫ ቦታዎች (ጉባኤ ቤቶች) አሠራርና አቀማመጥ ለትምህርት አሰጣጥና ለጤንነት ተስማሚ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

፯. የአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን መደበኛ መምህራን ጉባኤያቸውን ሳይፈቱ በየሳምንቱ እሑድ፤ በወርና በዓመት በዓላት የሚባለውን ቀለም (የሚደርሰውን ቃለ እግዚአብሔር) ለአገልጋዮች ካህናት ቀደም ብለው እንዲያስጠኑ መርሐ ግብር ያዘጋጃል፡፡

፰. ቤተ መጻሕፍት እንዲቋቋምና በሥርዓት እንዲያዝ ካህናቱም በተወሰነ ጊዜ በቤተ መጻሕፍቱ እየተገኙ በማንበብ እውቀታቸውን እንዲያሻሽሉና አእምሮአቸውም በትምህርት እንዲበለጽግ ለማድረግ አስፈላጊውን ሁሉ ይፈጽማል፡፡

፱. ለትምህርት የሚያገለግሉ በማዕከላዊ አሠራር በተዘጋጀ ሥርዓተ መሠረት የተመረጡ መጻሕፍትን የማቅረብ ኃላፊነት አለበት፡፡

፲. ተማሪዎች በየዕለቱና በየሰዓቱ በትምህርት ገበታ ላይ እየተገኙ ቸውን ትምህርት መከታተላቸውን ይቆጣጠራል፤ የትምህርት ችሎ
ለመገምገም
በተወሰኑ ጊዜያት ፈተና እንዲሰጣቸውና የፈተናውም ውጤት ተ
ለተማሪዎቹ እንዲገለጽ ያደርጋል፡፡

፲፩. ተማሪዎች እንዳለፈው ጊዜ ደበሎ ለብሰው እና ለምነው መማ
ችሉ በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ፣ ካልተቻለም በአካባቢው የ
አብያተ ክርስቲያናት በኅብረት አንድ ማዕከላዊ ትምህርት ቤት
መው ለመምህራን ደመወዝ፣ ለተማሪዎች ለምግባቸውና ለልብ
የሚሆን መጠነኛ የድጐማ በጀት እንዲመደብ ለማድረግ የሚ
ታቸውን ሁሉ ያስተባብራል፡፡

፲፪. መምህራንም ሆኑ ተማሪዎች አስፈላጊ በሚሆንበት የበዓላት ቀ
ቤተ ክርስቲያንን የማገልገልና የማስገልገል ግዴታ ያለባቸው
ማሳወቅና ማስፈጸም አለበት፡፡

፲፫. በእያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙት መምህራንና
በሰበካ ጉባኤው ጽ/ቤት ተመዝግበው መታወቂያ እንዲኖራቸው
ዚሁም እያንዳንዱ ተማሪ ትምህርቱን ፈጽሞ በሚሰናበትበት ጊ
ሁሩና በሰበካ ጉባኤው ጽ/ቤት አማካይነት የትምህርት ማስረጃ
ወረቀት እንዲሰጠው ያደርጋል፡፡

## አንቀጽ ፳

## የካህናት አገልግሎት ክፍል ሥራና ኃላፊነት

፩) ይህ ክፍል የቤተ ክርስቲያንን የውስጥ አገልግሎትና የክህነት ተ
የሚያጠቃልል ሆኖ ቆሰ ገበዙንና ሊቀ ዲያቆኑን እንዲሁም ሊቀ
ቱንና አጋፋሪውን እያስተባበረ ይሠራል፡፡

፪. ጸሎተ ቅዳሴውም ሆነ ሌላው መንፈሳዊ አገልግሎት ትክክለኛው ሥርዓት ይዞ እንዲካሄድ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፡፡

፫. ካህናት የንስሐ ልጆቻቸውን ከክህደትና ከኑፋቄ፣ ከክፉ ልማድና ለመጠበቅ እንዲችሉ ከትምህርት ክፍሉ ጋር በመተባበር በጥናት (ሴሚናር) እንዲሠለጥኑ ያደርጋል፤ ያስተምራል፤ ይቆጣጠራል፡፡

፬. ቀሳውስት፣ ዲያቆናትና መዘምራን ሌሎችም የቤተ ክርስቲያን
በየተግባራቸው ላይ በሰዓቱ ተገኝተው የተመደቡበትን የክፍል ሥ
ውንና መንፈሳዊ አገልግሎታቸውን ሳያጓድሉ በሥነ ሥርዓት መ
ቸውን እየተቆጣጠረ ሁኔታውን በየጊዜው ለጽ/ቤቱና ለአስተዳዳሪ
በማቅረብ ተገቢውን ይፈጽማል፡፡

፭. በሕገ ቤተ ክርስቲያን መሠረት ልዩ ልዩ መንፈሳዊ አገልግሎ
ሰናኑ ሁሉ በእኩልነትና በትክክል እንዲዳረስ ያደርጋል፡፡

፮. በቤተ ክርስቲያኑና በጠቅላላው በሰበካው ውስጥ የመንፈሳዊ አገልግሎትን፣
የካህናት ተልእኮንና ተግባርን በሚመለከት ጉዳይ ላይ ስለሚፈጠሩ
አንዳንድ ሁኔታዎች ጽ/ቤቱንና አስተዳዳሪውን እያሳሰበ አስፈላጊውን
ያስፈጽማል፡፡

፯. መስበክ ፣ ማጥመቅ ፣ ቀድሶ ማቁረብ ፣ ናዝዞ ማሰናበት በአጠቃላይ
አማንያን በሃይማኖት እንዲጸኑና በሥነ ምግባር እንዲጐለምሱ ማድረግ
የካህናት ተልእኮና ግዴታ መሆኑ እንዲታወቅ ያደርጋል፤ ካህናቱም ለዚህ
ሥራ ብቁ እንዲሆኑ ያዘጋጃል፡፡

፰. ያቃል ትምህርት ያጠና፣ ዳዊት የደገመ እና አምስቱ አዕማደ ምሥጢ
ራትን ያወቀ ግብረ ገብነቱና መንፈሳዊ ዝንባሌው በካህናትና በምእመናን
የተመሰከረለትን ለዲቁና ማዕረግ እንዲቀርብ ያደርጋል፡፡

፱. መዝገበ ቅዳሴ የተማረ ሰዓታት፣ ኪዳን፣ ሊጦንና መስተብቍዕ አጠናቅቆ
ያወቀ፣ ቅኔና ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን ያጠና ቅዱሳት መጻሕ
ፍትን ተርጉሞ ማስተማር የሚችል ግብረገብነቱና መንፈሳዊነቱ በሰበካው
ቤተ ክርስቲያን ካህናትና ምእመናን የተመሰከረለትን ዲያቆን የቅስና ማዕ
ረግ እንዲቀበል ለበላይ ማስታወሻ ያቀርባል፡፡

፲. ዓበይት በዓላት በሚከበሩበት ጊዜ ስለ በዓሉ አፈጻጸም መርሐ ግብር አዘጋ
ጅቶ ለሰበካው መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ(ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ)
ያቀርባል፤ ፕሮግራሙንም ያስፈጽማል፡፡

፲፩. ቀሳውስት፣ ዲያቆናት፣ መዘምራንና ሌሎችም የቤተ ክርስቲያኑ አገል
ጋዮች ከስካር ከአስነዋሪና ከመጥፎ ሥራ እንዲርቁ ይመክራል፤ አልባሌ
ቦታም እንዳይገኙ ይቆጣጠራል፡፡

፲፪. በቅዳሴ ጊዜ ከቤተ ክርስቲያን መውጣት፣ ወዲያ ወዲህ መመላለስና
እርስ በርስ መነጋገር የማይገባ መሆኑን ለምእመናን ትምህርትና ምክር
ይሰጣል፡፡

፲፫. በሰንበቴና በዝክር ጽዋዕ ሳቢያ ከቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ውጭ በአንድ
አንድ አካባቢ በአምሳለ ታቦት ጃንጥላ ይዘውና መብራት አብርተው
በየመንገዱና በየመንደሩ በሚዘዋወሩት ካህናትና ምእመናን ላይ ጥብቅ
ቁጥጥር ያደርጋል፤ ምእመናኑም አድራጐቱ ከሃይማኖት ሥርዓት ውጭ
መሆኑን አውቀው ከእንደዚህ ዓይነት ተግባር እንዲርቁ ትምህርትና
ምክር ይሰጣል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፡፡

፲፬. ሥራቸው ያልታወቀና ክህነታቸው ያልተመረመረ ግለሰቦች ቄስ ወይም
መነኩሴ በመምሰል ለምእመናን የንስሐ አባት እየሆኑ በቤተ ክርስቲያን
አገልግሎት ላይ ችግር እንዳይፈጥሩ ይቆጣጠራል፤ ለምእመናንም ትምህ
ርት ይሰጣል፡፡

፲፭. በስመ ዲያቆን፣ በስመ ቄስና በስመ መነኩሴ ማዕረገ ክህነት ያላቸው
ለመሆኑ ያልታወቁ ካህናት በውክልና እንዳይቀድሱ እና የውስጥ አገልግ
ሎት እንዳይፈጽሙ በጥብቅ ይቆጣጠራል፡፡

፲፮. ምእመናን በሰንበትም ሆነ በበዓላት ቀናት ልጆቻቸውን ይዘው በመምጣት
የቤተ ክርስቲያኒቱን እምነትና ሥርዓት እንዲያጠኑ ለማድረግ ለንስሐ
አባቶች መመሪያ ይሰጣል፡፡

፲፯. የክርስትና አባቶች ወይም እናቶች በአንቀጸ ጥምቀት በተደነገ
በገቡት ቃል ኪዳን መሠረት ለክርስትና ልጆቻቸው የቤተ ክር
ሥርዓትና እምነት የማስተማር ኃላፊነትና ግዴታ ያለባቸው መ
ያሳውቃል፡፡

፲፰. ክርስቲያን የሆኑ ሁሉ እናት፣ አባት፣ ባል፣ ሚስት፣ ልጅ፣
እህት ዘመድ ወዳጅ በሞተባቸው ጊዜ ከመጥፎ ባሕልና እምነ
ጉጂ ልማድ ፊትና ፀጉር እየነጩ ልብስ እየቀደዱ ደረት እየ
አስለቃሽ እያቆሙ ሙሾ እያወጡና እየዘለሉ ማልቀስ የተወገዘ
ፈጽሞ እንዲቀር አመች በሆነ ቦታና ጊዜ ሁሉ ለምእመናን በ
እንዲገለጽ ያደርጋል፤ አፈጻጸሙንም ይቆጣጠራል፡፡

## <u>አንቀጽ ፳፩</u>

## <u>የሰንበት ት/ቤት ክፍል ሥራና ኃላፊነት</u>

ስለ ሰንበት ት/ቤት ወጣቶች በቅዱስ ሲኖዶስ ፈቃድ
ደንብና መመሪያ እየተከታተለ የሰበካው የሰንበት ት/ቤት ክ
የተዘረዘሩትን ተግባሮች ያከናውናል፡፡

፩. የሰንበት ት/ቤትን በሰበካው ቤተ ክርስቲያን ያቋቁማል፥ ያደረ
በሰበካው ከአራት እስከ ሰላሣ ዓመት የዕድሜ ክልል የሚገኙት
ወጣቶች የሰንበት ት/ቤት አባላት እንዲሆኑና ዲያቆናት በመማ
ስትና መምህራን በማስተማር በሰንበት ት/ቤቱ እንዲሳተፉ ያደ

፪. ለሕፃናትና ለወጣቶች እንደየዕድሜያቸው ክልል በመከፋፈል በ ደረጃ በሚወጣው ሥርዓተ ትምህርት መሠረት ትምህርት መሰ ይከታተላል::

፫. በሰንበትና በሌሎችም ዓበይት በዓላትና አመቺ ቀናት የዕለትና መርሐ ግብር በማውጣት የቤተ ክርስቲያን ሕግና ሥርዓት፣ የ ትምህርት፣ የቅዳሴ ተሰጥዖና የቅዱሳት መጻሕፍት ጥናት እን ያደርጋል::

፬. ሕፃናትና ወጣቶች ከኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት እንዳይወጠ ክርስቲያንን ሕግና ሥርዓት እንዲያውቁና እንዲያከብሩ፥ ግብረ ሆኑ ከአስተዳደሩ ጋር በመተባበር በቅርብ እየተከታተለ ያስተ ይመክራል፤ ይቆጣጠራል::

፭. ለምዕመናን ትምህርትን የሚሰጡ መንፈሳዊ መዝሙራትን እ ለትና የዘወትር መርሐ ግብር ያዘጋጃል::

፮. ወጣቶች መንፈሳዊ ዕውቀታቸው እንዲዳብር ሥዕሎችና ልዩ ማሪያ መሣሪያዎች የሚገኙበት ቤተ መጻሕፍትን ያቋቁማል::

፯. ከሰንበት ተማሪዎች በበዓላትም ሆነ በአጋጣሚ ጊዜ በትያትር ርበው መንፈሳዊ ዝግጅት በቅድሚያ ለሰበካ አስተዳደር ጉባኤ

ከተመረመረና ከተጠና በኋላ ሲፈቀድ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል::

፰. የሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች በትያትርም ሆነ በማናቸውም ሁኔታ የሚሰበ ስቡት ገንዘብ ለአጥቢያው ሰበካጉባኤ ገንዘብ ቤት ገቢ ይሆናል፤ ለሚያስ ፈልጋቸው ወጪ ጥናቱ ለአስተዳደር ጉባኤ ቀርቦ ሲፈቀድ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል::

፱. ቀሳውስት የንስሐ ልጆቻቸው ልጆች መንፈሳዊውን ትምህርት እንዲከ ታተሉ ወላጆችም ልጆቻቸው በሰንበት ት/ቤት ተመዝግበው መንፈሳዊውን ዕውቀት እንዲቀስሙ ማድረግ ክርስቲያናዊ ግዴታቸው መሆኑን ያሳውቃል::

፲. የሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች መንፈሳዊውን በዓል በሚያከብሩበት ጊዜ የቤተ ክርስቲያናችንን ሥርዓትና ባሕል በተከተለ ሁኔታ የመለያ ልብስ (ዩኒፎርም) እንዲዘጋጅላቸው ያደርጋል::

፲፩. በሰበካ ጉባኤ ወይም ከዚያ በላይ በሆነ አካል ካልታወቀና በጽሑፍ ካልተፈቀደ በስተቀር በሰንበት ት/ቤት ስም የአዳር መርሐ ግብር እንዳ ይደረግ በጥብቅ ይቆጣጠራል::

፲፪. ከስብከተ ወንጌልና ከመንፈሳዊ ት/ቤት ክፍሎች ጋር በመተባበር መም ህራንን እየጋበዘ ለሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች ብቃትና ጥራት ያለው ትምህርት እንዲሰጣቸው ያደርጋል::

## አንቀጽ ፳፪

## የእቅድና ልማት ክፍል ሥራና ኃላፊነት

፩. ያጭርና የረጅም ጊዜ ዕቅድ በማውጣት ልዩ ልዩ የሥራ እቅዶች ማስፈጸ ሚያ የገንዘብ፣ የዕቃ፣ የዕውቀትና የጉልበት ርዳታና መዋጮ ከምእመናን፣ ከልዩ ልዩ ማኅበርና ድርጅት ይጠይቃል::

፪. ለሰበካው የገቢ ምንጭ የሚገኝበትን ተስማሚ የሥራ መስክ ያዘጋጃል፣ እንዲሁም ለንዋየ ቅድሳት፣ ለመጻሕፍት፣ ለአልባሳትና ለሌላም የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚውልና ለገበያ የሚቀርብ የቅርፃ ቅርፅና የተግባረ ዕድ ሥራ ያቋቁማል::

፫. በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን የሚገኙት ካህናትና ምእመናን የሰንበት ት/ቤት ወጣቶችም ያላቸውን ዕውቀት፣ የጥሬ ገንዘብ(ሀብት) ልዩ ልዩ ዕቃዎችና የሰውን ጉልበት ጭምር በማስተባበር ለቤተ ክርስቲያኑ ልማት ሥራ እንዲውል ያደርጋል::

፬. ካህናት በትርፍ ጊዜአቸው ራሳቸውን ለመርዳት እንዲችሉ የገቢ ምንጭ ለማስገኘት የሚመለከታቸውን በማስተባበር ከቤተ ክርስቲያኑ አገልጋዮች ካህናት ውስጥ እየሠለጠኑ በየዝንባሌያቸው እንዲሠማሩና የምርት ውጤት እንዲያስገኙ ያደርጋል::

፭. ከልማቱ የሚገኘው ገቢ በሰበካ ጉባኤው ካርኒ እየተሰበሰበና በገንዘብ ቤቱ

እየተጠቃለለ በቤተ ክርስቲያኑ ስም በተከፈተ የባንክ ሒሳብ ገቢ ይሆ

፮. የሥራውንም ውጤት በሚመለከት በየሦስት ወር ለሰበካ ጉባኤው ሪፖ ያቀርባል:

## አንቀጽ ፳፫

## የምግባረ ሠናይ (በጐ አድራጐት)ክፍል ሥራና ኃላፊነት

፩. ይህ ክፍል በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙትን የሰንበቴ፣ የዕድር፣ የልዩ ልዩ ምግባረ ሠናይ ማኅበራትን እንዲሁም በጐ አድራጊዎች ግ ችን በማስተባበር አሳዳጊ ያጡ ሕፃናትን ጧሪ ቀባሪ የሌላቸውን ሽማ ዎችና አሮጊቶችን፥ ድሆችንና ችግረኞችን የሚረዳ ክፍል ነው፡፡

፪. በሰበካው ያሉት ችግረኞች በተደራጀ አቋም የሚረዱበትንና ራሳቸው የሚችሉበትን መንገድ ለመፈለግ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሀ ድርጅቶችን እያስተባበረ ይሠራል፡፡

፫. ለመሥራት ችሎታና እውቀት ያላቸው ችግረኞችን መርጦ በራስ አ ፕሮግራም ሠርተው እንዲጠቀሙ ከሚመለከታቸው ሁሉ ጋር በመነ በመጻጻፍ ሁኔታውን ተከታትሎ ያስፈጽማል፡፡

፬. መንፈሳዊና ሥጋዊ አኗኗራቸው የተሻሻለ እንዲሆንና ቀቢጸ ተስፋም እንዳይሰማቸው ከካህናቱ መካከል በእውቀቱና በግብረ ገብነቱ የተሻለ ካህን ተመርጦ በተወሰነ ሰዓት እንዲያስተምራቸውና እንዲመክራቸው የትምህርት መርሐ ግብር ያዘጋጃል፡፡

፭. በሰንበት ፣በወርና በዓመት በዓላት በጸሎተ ቅዳሴ ጊዜ በትምህርተ ወንጌል ሰዓትና ሌላውም መንፈሳዊ አገልግሎት ሲካሄድ በዓውደ ም፡ እየተዘዋወሩ ድምጽ በማሰማት እንዳያስቸግሩ አመች በሆነ ቦታ በአ አሰባሰቦ እርዳታ እንዲለግሱአቸው በጐ አድራጊ ምእመናንን ያስተባ፡

፮. በሰበካው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወላጅ ወይም አሳዳጊ የሌላቸው ሕ ጊዜያዊና ዘላቂ እርዳታ የሚያገኙበትን መንገድ እያጠና ለሰበካ መን ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) በማቅረብ አፈጻጸሙን ይከታተላል፡፡

፯. ምእመናንን በጐ አድራጊ ግለሰቦችንና ድርጅቶችን በማስተባበር ች ኞች፣ ጧሪና ረዳት የሌላቸው ሽማግሌዎችና ባልቴቶች በቤተ ክርስ አካባቢ መጠለያ እንዲያገኙ ያደርጋል፤ ጤናቸውንም ይንከባከባል፡፡

## አንቀጽ ፳፬

## የሕግና ሥነ ሥርዓት ክፍል ሥራና ኃላፊነት

፩. በቅዱስ ሲኖዶስ የሚወጡት ድንጋጌዎች፣ በመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የሚወጡትን ውሳኔዎችና መመሪያዎች ለሰበካው ጉባኤ ኃላፊዎችና በጠቅላላው ለካህናትና ለምእመናን በቤተ ክርስቲያን ሕግና ሥርዓት መሠረት ሕጋዊ መመሪያና መግለጫ እየሰጠ እንዲያው ቁትና እንዲያጠኑት የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

፪. በሰበካው ውስጥ በካህናትም ሆነ በምእመናን መካከል የሚፈጠር አለመግ ባባት ቢኖር ወደ ክስና ሙግት ደረጃ ሳይደርስ እርስ በርስ በመተራረም በይቅርታና በእርቅ እንዲወገድ የተቻለውን ሁሉ ያደርጋል፡፡

፫. የክሱ አቤቱታ ሕገ ቤተ ክርስቲያንን የሚመለከት ሆኖ ሲገኝ የከሳሹና የተከሳሹን የሕግ መብት በመጠበቅ የሁለቱንም ወገን ማስረጃዎች በጥንቃቄ ተመልክቶ በዚህ ቃለ ዓዋዲ በአንቀጽ ፳፫ መሠረት በቀላል ጥፋቶች ላይ ቅጣት ይወስናል፤ የከባድ ጥፋቶችን ጉደይ ግን ከውሳኔ ሐሳብ ጋር ለሰበካው አስተዳደር ጉባኤ ያቀርባል፡፡

፬. በክብረ በዓል ቀን ከሰበካው አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት በሚሰጠው መመሪያ መሠረት እንደ አስፈላጊነቱ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መንግሥ ታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የበዓሉን ሥነ ሥርዓት ያስከብራል፡፡

፭. ለምእመናን መንፈሳዊ ሕይወት የማይጠቅሙና ለቤተ ክርስቲያን አገል ግሎት የማይውሉ ሸቀጣ ሸቀጦች በዓፀደ ቤተ ክርስቲያን ቅጽር ውስጥ እንዳይሸጡና ሌሎችም የቤተ ክርስቲያን ሕግና ሥርዓት የሚቃረኑ ተግባራት እንዳይፈጸሙ ከስብከተ ወንጌል እና ከሰንበት ት/ቤት ክፍሎች ጋር በመተባበር ይከላከላል፤ ሥነ ሥርዓቱንም ያስጠብቃል፡፡

፮. ማናቸውንም መንፈሳዊና ሥጋዊ ሕግ-ነክ ጉዳዮች ይከታተላል ፤ ለቤተ ክርስቲያኑ አስተዳደርም የምክር አገልግሎት ይሰጣል፡፡

## አንቀጽ ፳፭

## የንብረት፣ የዕቃ ግምጃ ቤትና የታሪካዊ ቅርስ ክፍል ሥራና ኃላፊነት

፩. ከታቦተ ሕጉ ጀምሮ የቤተ ክርስቲያን ንዋየተ ቅድሳት፣ አልባሳት፣ መጻሕፍትና ልዩ ልዩ ንብረቶች ሁሉ ለዚሁ ሥራ ተመርጦ በተመደበ ካህን (ቀሰ ገበዝ) በጥንቃቄ እየተመዘገቡ እንዲጠበቁ ያደርጋል፡፡

፪.የሰበካ ጉባኤውን አላቂና ቀዋሚ ዕቃዎችን የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን በየዓይነታቸው ለይቶ ይመዘግባል፡፡

፫. ወጪ ሆነው የሚታደሉትንና የሚሰጡትን ዕቃዎችና ንብረቶችን በ; ያከፋፍላል፤ የታደሉትም ሥራ ላይ መዋላቸውንና መጠበቃቸውን ; ጠራል፤ የሚመለሱትንም መርምሮ ይረከባል፡፡

፬. ለቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጣዊ አገልግሎት የሚያስፈልጉትን ነገሮች ፤ እንዲሟሉ ያደርጋል፡፡

፭. በቤተ ክርስቲያን ታሪካዊ ቅርሳ ቅርሶች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ አ ሳጊውን ጥበቃ ያደርጋል፤ ለጐብኝዎችና ለታሪክ ጸሐፊዎችም እንደ አድርጐ ምቹ በሆነ ሥፍራ በሥነ ሥርዓት ያዘጋጃል፡፡

፮. ጥንታውያን የብራና መጻሕፍት፣ ሥዕሎች፣ አልባሳት፣ ከወርቅ ፣ ከነሐስ፣ ከብረትና ከዕፀ የተቀረጹ መስቀሎችና ልዩ ልዩ ንዋያተ ቅ እንዲሁም የባህልና የወግ ዕቃዎች ለብል፣ ለዝገት፣ ለፍሳሽ፣ ለእሳት ለመሳሰሉት አደጋዎች እንዳይጋለጡ፦

  ሀ) ለቅርሳ ቅርስ አጠባበቅ አመች የሆነ ዕቃ ቤት ያዘጋጃል፡፡

  ለ) ቅርሳ ቅርሱን በኃላፊነት የሚጠብቁ ሠራተኞችና አስጐ እንዲመደቡ ያደርጋል፡፡

  ሐ) በየበጀት ዓመቱ መጨረሻና የቅርሳ ቅርስ ኃላፊ ገ በሚደረግበት ጊዜ ሁሉ ማንኛውም ቅርስ እየተ እየተመረመረ ውጤቱን ደረጃውን ጠብቆ እስከ ፓትርያርክ ድረስ መግለጽ ግዴታው ይሆናል፡፡

  መ) ከአገር ውስጥና ከውጭ አገር ጐብኝዎች ሲመጡ ከጠቅላ. ክህነት በየጊዜው በሚሰጠው የአፈጻጸም መመሪያና የክፍያ መሠረት ከጐብኝዎች ገቢ እንዲገኝ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡

  ሠ) ይኸው ከጐብኝዎች የሚገኘው ገቢ በሕጋዊ ካርኒ እየተ ከቤተ ክርስቲያኑ ጠቅላላ ሒሳብ ጋር እንዲያዝ ያደርጋል፡

፯. ለአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ንብረትና ታሪካዊ ቅርሳ ቅ ግምጃ ቤት ሆኖ የሚመደበው ካህን የገንዘብ ጉድለት ያልተገኘበት በንብረት ማባከንም ሆነ በሌላ ወንጀል ተከሶ በጉባኤ ያልተወሰነበት፣ በፍርድ ቤት ያልተፈረደበትና በቂ ተያዥ ያለው መሆኑን ያረጋግጣ

፰. ረዘም ላለ ዘመን የቆዩ አልባሳት፣ ንዋያተ ቅድሳትና መጻሕፍት ከ. ሎት አርጌው ዓይነታቸው ሳይለወጥ ጥገና እየተደረገላቸው በቅርስነት ተከብረው እንዲቀመጡ ያደርጋል፡፡

፱. የቤተ ክርስቲያኒቱ ቅርሶች በልዩ ልዩ ምክንያት በውሰት እንዲወሰዳ ጠየቅበት ጊዜ የክፍሉ ሊቀ ጳጳስ ፈቅዶና መንበረ ፓትርያርኩ አው የማስፈጸሚያ ትእዛዝ ሲደርሰው ሕጋዊ በሆነ ደረሰኝ አስፈርሞ ለተወ ጊዜ በትውስት እንዲሰጥና እንዲመለስ ያደርጋል፤ ካልተመለሰ ለሚወ ከተው ባለሥልጣን ማስታወሻ በማቅረብ ወደ ነበረበት ቦታ እስኪመለ ድረስ እስከ መጨረሻው ተከታትሎ ያስፈጽማል፡፡

፲. ጠቅላላ የቤተ ክርስቲያኑ ንብረቶች በየዓመቱ መጨረሻ እየተቆጠሩ ዛቸውንና በጥንቃቄ መቀመጣቸውን ያረጋግጣል፤ ያሉትንና የሌሉትን ለይቶ በመዘርዘር ለሰበካው አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት ሪፖርት ያቀር

## አንቀጽ ፳፮

## የሒሳብ ክፍል ሥራና ኃላፊነት

፩. የሒሳብ መዛግብትን በተሟላ ሁኔታ አዘጋጅቶ ገቢና ወጪውን ይመዘ ግባል፡፡

፪. ገቢው በሕጋዊ የሒሳብ አያያዝ ደንብ መሠረት በሕጋዊ ደረሰኝ መግባ ቱንና ወጪውም ሕጋዊ የወጪ አርእስቶችን ጠብቆ በደንበኛ የወጪ ማዘዣና ማስመስከሪያ ሰነድ መውጣቱን እያረጋገጠና እየተከታተለ ይሠራል፡፡

፫. በየወሩ መጨረሻ ሒሳቡን በመዝጋት የወሩን ገቢ፤ ወጪውንና ከወጪ ቀሪውን በሠንጠረዥ እያዘጋጀ ለጽ/ቤቱ ያቀርባል፡፡

፬. ማናቸውም የገንዘብ ወጪ ከተፈቀደውና ከተወሰነው በጀት ጣራ በላይ እንዳያልፍ ይቆጣጠራል፤ ይጠብቃል፡፡

፭. በጀት በሚደለደልበት ጊዜ ገንዘብ መኖሩን ያረጋግጣል፡፡

፮. የበጀት ዓመቱ ከማለቁ ከሁለት ወራት በፊት በባንክና በሳጥን ያለውን ገንዘብ የየወሩን ገቢ ገምግሞ የተከታዩን ዓመት በጀት በመሥራት የበጀ ቱን ዝርዝር ለሰበካው አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት ያቀርባል፡፡

፯. ዓመታዊም ሆነ ወርኃዊ ሒሳብ እንዲመረመር ሲታዘዝ የገቢና የወጪ ሰነዶችን በማቅረብ ያስመረምራል፡፡

፰. የሒሳብ ሰነዶችንና ቼኮችን በጥንቃቄ ይይዛል፡፡

፱. የገንዘብ ገቢና ወጪ ሰነዶች(ሞዴሎች) በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት የበላይ ተቆጣጣሪነትና በመን በረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት ኃላፊነት ታትሞ በሚወጣ በአንድ ዓይነት ደረሰኝ (ካርኒ) ብቻ የሚሠራ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

## አንቀጽ ፳፪

## የገንዘብ ቤት ሥራና ኃላፊነት

፩. ገንዘብ ያዥው ለሰበካው ቤተ ክርስቲያን የገባውን ገንዘብ ሁሉ በዚሁ ቃለ ዓዋዲ በአንቀጽ ፶፮ ንዑስ አንቀጽ ፬ በተጠቀሰው ሕጋዊ ደረሰኝ(ካርኒ) ይቀበላል::

፪. የተቀበለውን ገንዘብ በቤተ ክርስቲያኑ ስም በዕለቱ ባንክ ያስገባል፤ ገንዘቡን የተቀበለው ጊዜ(ሰዓት) ካለፈ በኋላ ከሆነ ወይም ባንክ ዝግ በሆነ በት ቀን ከሆነ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ጋር በመፈራረም ገንዘቡ በጊዜያ ዊነት እንዲቀመጥናገንዘብ ቤቱ እንዲታሽግ ያደርጋል::

፫. በአካባቢው ባንክ ከሌለ አስተደደር ጉባኤው በሚወስነው ቦታ ሊያስቀምጥ ይችላል::

፬. በካዝና ስለሚቀመጠው መጠባበቂያ ሒሳብ እንደጊዜውና እንደአካባ( እየታየ ከበላይ በሚሰጠው መመሪያ ይወሰናል::

፭. ለማናቸውም የገንዘብ ወጪ ሕጋዊ ትእዛዝ ሲደርሰው በደንበኛ የወ( ማስመስከሪያ ሰነድ (ቫውቸር) አስፈርሞ ይከፍላል::

፮. ገቢና ወጪውን በተለይ በተዘጋጀ የገቢና የወጪ መዛግብት ላይ ይ( ግባል፤ በየወሩ መጨረሻ በጠቅላላ የገባውንና የወጣውን ገንዘብ ልክ ዚሁም ከወጪ ቀሪውን ከሒሳብ ክፍሉ መዛግብት ጋር እያመሳከረ ( በጥንቃቄ መዝግቦ ይይዛል::

፯. አስተዳዳሪው ማዘዣ ካልጻፈ በስተቀር አንዳችም ገንዘብ ወጪ ማድ( አይችልም፤ ሆኖም አስተዳዳሪው በሌለ ጊዜ በም/ሊቀ መንበሩ ትእ የታወቀውን፤ የተወሰነውንና የተመደበውን የወር ወጪ ብቻ ሊያወጣ ይችላል::

## አንቀጽ ፳፫

## የቁጥጥር ክፍል ሥራና ኃላፊነት

፩.ገቢና ወጪውን በየወሩ ተቆጣጥሮ ገንዘቡ በባንክ መቀመጡን ያረጋግ

፪. ገቢና ወጪ የተደረገባቸው ካርኒዎችና ሰነዶች ሕጋዊ መሆናቸውን ( ምራል::

፫. ከሰበካ ጉባኤው ንብረት መዝገብ ጋር አስተያይቶ በዕቃ ግምጃ ቤቱ ኃፊነት የሚገኙትን ቋሚና አላቂ ዕቃዎችን በየመልካቸው ለይቶ በአ ግሎት ያለቁትን፣በአያያዝ የተበላሹትን፣ የጐደሉትንና የተረፉትን እ ዚሁም ያልተመዘገቡትን ንብረቶች ሁሉ እያስቆጠረ ዓይነቱና ብዛቱ በሠንጠረዥ ተዘጋጅቶ መመዝገቡን እያመሳከረ ይቆጣጠራል::

፬. የሒሳቡ አያያዝና የንብረቱ አጠባበቅ ትክክል መሆኑንና አለመሆኑን በዝርዝር መዝግቦ በየሦስት ወር ለሰበካው አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት መግለጫ ያቀርባል::

፭. በገንዘብ አያያዝና በንብረት አጠባበቅ ጉድለት ቢገኝ ጉድለት ወይም ጥፋት ያደረሰውን ግለሰብ መተማመኛ አስፈርሞ ለሰበካው አስተዳ( ጉባኤ ጽ/ቤት ያቀርባል::

፮. በሰበካ ጉባኤ የተመዘገቡት የአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ምእመናን የ( ሉት አስተዋጽኦ በቃለ ዓዋዲው መሠረት መክፈሉንና ማናቸውም የ( ክርስቲያኒቱ ልዩ ልዩ ገቢ በትክክል መግባቱን ይቆጣጠራል::

፯. በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ለደመወዝና ለሥራ ማስኬጃ ለወርና ለዓመት ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ እንዳይሆን ይቆጣጠ(

፰. በሰበካው ቤተ ክርስቲያን የሥራ ዘርፎች የሚካሄዱት ሥራዎች ሁሉ በወቅቱ መከናወናቸውን እየተቆጣጠረ ሥራው የሚመለከታቸውን ሠ( ኞች በማሰባሰብ ወይም በየክፍሉ በመዘዋወር እንደአስፈላጊነቱ ስለ ሐ( አያያዝና የሞዴሎች አጠቃቀም ተገቢውን ጥናትና መመሪያ ይሰጣል::

፱. በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን የሚገኙት የስእለትና የሙዳየ ምፅዋት ሣጥ ኖች ምልክትና መለያ ቁጥር እየተሰጣቸው ብዛታቸው የታወቀና የተቀመ ጡበት ቦታ ግልጽና አስተማማኝ መሆኑን ያረጋግጣል፤ ያልተመዘገቡና ያልታወቁ ሣጥኖችም ሆኑ ሌሎች የገንዘብ መሰብሰቢያዎች ሁሉ በቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለመኖራቸውን በጥብቅ ይቆጣጠራል::

፲. የስእለትና የሙዳየ ምፅዋት ሣጥኖች በሥራ ላይ ከመዋላቸው በፊት በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በተመረጡ አባላት፣አስተዳዳሪው፣ሒሳብ ሹሙና ተቆጣጣሪው በሚገኙበት የጋራ ፊርማ መታሸጋቸውንና ሲከፈቱም የፈረ ሙት አባላት ሁሉ መገኘታቸውን ይከታተላል::

፲፩. በዓውደ ምሕረቱም ሆነ በሌላ ቦታ ሙዳየ ምጽዋትና ጥላ በማዞር ስጋጃ በማንጠፍ ወይም በሌላ መንገድ የሚሰበሰበው ማናቸውም ገንዘብና ልዩ ልዩ ስጦታ ሁሉ በአግባቡ እየተመዘገበ በቤተ ክርስቲያኑ ካርኒ (ደረሰኝ) ገቢ መሆኑን ያረጋግጣል::

፲፪. በስእለትና በሌላም ምክንያት ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጡት እንስሳት፥ ብርናወርቅ እንዲሁም ልዩ ልዩ ንብረቶች ሁሉ ግምታቸው እንዲታወቅና በሕጋዊ መንገድ ገቢ እንዲሆኑ አስፈላጊውን ጥረት ያደርጋል።
፲፫. ከንብረት ክፍሉ ጋር በመተባበር የቤተ ክርስቲያኑን ንብረት በየዓመቱ እያስቆጠረና የመዘገበ (ኢንቬንቶሪ በማድረግ) የጐደለውንና የጨመረውን አረጋግጦ ለሰበካው አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት ሪፖርት ያቀርባል።

## አንቀጽ ፳፱

## የሕንፃ ሥራ፣ ጥገናና እድሳት ክፍል የሥራ አፈጻጸም

፩. ይህ ክፍል ቤተ ክርስቲያንን፣ ቤተልሔምን፣ ትምህርት ቤትን፣ የመሰብሰቢያ አዳራሽን፣ የሰንበት ት/ቤትን፣ የካህናትና የእንግዶች ማረፊያ ቤትን፣ ቅጽረ ቤተ ክርስቲያንን ሌሎችንም እንደ አስፈላጊነታቸው ሊሠሩ የሚገባቸውን እቅዶች አጥንቶ ለሰበካው አስተዳደር እያቀረበና እያስፈቀደ በዚህ ቃለ ዓዋዲ አንቀጽ ፲፪ ንዑስ አንቀጽ ፲፰ መሠረት ከሚቋቋመው የሕንፃ አሠሪ ኮሚቴ ጋር በመተባበር የሚሠራ ክፍል ነው።
፪. ስለ ሕንፃ ሥራ፣ ጥገናና እድሳት አፈጻጸም ቅዱስ ሲኖዶስ በሚያወጣው ልዩ የሕንፃ ሥራ ደንብና መመሪያ የሚወሰን ይሆናል።
፫. የሕንፃ አሠሪ ኮሚቴ በሚቋቋምበት ጊዜ ከቤተ ክርስቲያኑ አስተዳደር ጽ/ቤት መመሪያ እየተቀበለ ካህናትና ምእመናን በጉዳዩ እንዲያስቡበት አስፈላጊውን ቅስቀሳ ያደርጋል፥ ትምህርት ይሰጣል።
፬. ለቤተ ክርስቲያኑ ሕንፃ ሥራ የሚውል የገንዘብና የቁሳቁስ እርዳታ የሚገኝበትን መንገድ እያጠና በሚቋቋሙት የሕንፃ አሠሪ ኮሚቴዎች አማካይነት እርዳታው እንዲሰበሰብ ያደርጋል።

፭. ለቤተ ክርስቲያኑ ሕንፃ ሥራ የሚያስፈልጉትን የገንዘብና የንብ ወጪ ማድረጊያ ካርኒዎችን፣ ሰነዶችንና መዛግብትን በጠቅላላ የ የጽሕፈት መሣሪያዎች ሁሉ ከኢትዮጵያው ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ጽ/ቤት በደረሰኝ እየተረከበ ለተቋቋመው ኮሚ አስፈላጊነቱ ያከፋፍላል።
፮. ለሕንፃው ሥራ እርዳታ ለሚለግሱ በጐ አድራጊ ግለሰቦችና ድር ከኢትዮጵያው ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት የሚተላለ የጥያቄና የትብብር ደብዳቤዎች ለሚመለከታቸው ሁሉ እንዲደር ያደርጋል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል።
፯. የሕንፃ ሥራ ዓቢይ ኮሚቴው በሚያደርገው ስብሰባ ሁሉ እየተገ ራው ሂደት የተደረሰበትን ፍሬ ሐሳብ ለኢትዮጵያው ሰበካ መንፈ ዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት በሪፖርት ያቀርባል።
፰. በሕንፃ ቤተ ክርስቲያኑ ስም ከአካባቢው ምእመናን የሚሰበሰበ ልዩ በጐ አድራጊ ድርጅቶች የሚለገሰው ገንዘብ በቤተ ክርስቲያ በተከፈተ የባንክ ሒሳብ ቁጥር ተለይቶ መቀመጡን ያረጋግጣል በሚሆንበት ጊዜም በአንቀጽ ፲፫ ንዑስ አንቀጽ ፱ መሠረት መ ይከታተላል።
፱. የሕንፃው ሥራ ተጠናቅቆ ካበቃ በኋላ የሕንፃው ሥራና ከሕንፃ ግንኙነት ያለው የንብረትና የገንዘብ ገቢና ወጪ እንዲሁም ከወ ሒሳብ በምርመራ (በኦዲት) ተጣርቶ ለቤተ ክርስቲያኑ ገንዘብ ንብረት ክፍል ገቢ መሆኑን ይከታተላል፤ ያረጋግጣል።
፲. የሙታን መቃብር ሥርዓት በሌለው ልሽ ሥራና በሐውልት ግ እየተጣበበ የመጣውን ቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ችግር ለማቃለል ይህ ዓይነቱ አሠራር ቀርቶ በምትኩ የተሻሻለ አሠራር እንዲኖር ረግ ባለሙያዎችን እያማከረና እቅዱን ለአስተዳደር ጉባኤ እያቀ ሰን በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል።
፲፩. ለብዙ ዓመታት የቆዩ የሙታን አጽሞች በክብር ተሰብስበው የሚያርፉበትን ቤት እንዲዘጋጅና እንዲጠበቅ ያደርጋል።
፲፪. በቅጽረ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙት ክፍት ቦታዎችና ለመቃብር ሉት ስፍራዎች ሁሉ በጽዳት እንዲጠበቁና የተለያዩ የዕጽዋት ችንና አበቦችን ያስተክላል፤ መካነ ጸሎቱን ዓውደ ምሕረቱን ብራል።

## አንቀጽ ፴

## የእስታቲስቲክስ ክፍል ሥራና ኃላፊነት

፩. በኢትዮጵያው ቤተ ክርስቲያን ነዋሪ ለሆኑ ምእመናን ቀዋሚ መ ሆነው የሚያገለግሉትን፦
ሀ) መዝገበ ልደትና ጥምቀት

ለ) መዝገበ ሕያዋንና መዝገበ ሙታን እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ መዛግብትን ሁሉ ያዘጋጃል፡፡

፮. የአጥቢያውን ቤተ ክርስቲያን ሙሉ ስምና አድራሻ፣ የትክል ዓይነትና ዘመን፣ የሕንፃውን አሠራር ቅርጽና ዓይነቱን፣ ቁመቱንና ስፋቱን አይቶና አጣርቶ ባለሙያ እያማከረ ይመዘግባል፡፡

፯. የአጥቢያውን ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ካህናት፣ ቀሳውስት፣ መምህራን፣ ሰባክያን፣ ዲያቆናት፣ መዘምራንና ልዩ ልዩ ሠራተኞች ብዛት እንዲሁም የምእመናንን ብዛት በጧሱና በቤተሰብ በዕድሜና በፆታ ለይቶ እንዲመዘገብ ያደርጋል፡፡

፰. በሰበካው የጉባኤ መምህር ካለ ስሙንና የተማሪዎችን ብዛት የትምህርቱን ዓይነት በመግለጽ ለይቶ ይጽፋል፤ እንደዚሁም የሰንበት ት/ቤትን ተማሪዎች ብዛት የሚማሩትንም የትምህርት ዓይነት ይገልጻል፡፡

፱. ሕፃናት አርባ ቀንና ሰማንያ ቀን ሞልቶአቸው በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት መሠረት ጥምቀተ ክርስትና ሲቀበሉ በመዝገበ ልደትና ጥምቀት እንዲሁም በአጠቃላይ ለአጥቢያው ካህናትና ምእመናን በተዘጋጀው መዝገበ ሕያዋን ላይ ይመዘግባቸዋል፡፡

፲. ከዚህ ዓለም በሞት የሚለዩትን የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮች ስማቸውን በመዝገበ ሙታን ያሰፍራል፡፡

፲፩. በዓመቱ መጨረሻ በጠቅላላ በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን በነዋሪነት የተመዘገቡትን ክርስቲያኖች ብዛት ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩትን ብዛት እንዲሁም የተወለዱትንና በዓመቱ ውስጥ በሥራ ዝውውርም ሆነ በልዩ ልዩ ምክንያት ወደ አጥቢያው ቤተ ክርስቲያን በነዋሪነት አዲስ የመጡትንም ሆነ ወደ ሌላ አጥቢያ የሄዱትን ክርስቲያኖች ሁሉ በጥንቃቄና በጥራት መዝግቦ ለሰበካው አስተዳደር ጽ/ቤት ያቀርባል፡፡

፲፪. የሰበካውን የሰው ኃይልና የገንዘብ ኃይል በየዓመቱ እየመዘገበ ካለፈው ዓመት ጋር ያለውን ልዩነት እያነፃፀረ በሠንጠረዥ ወይም በሥዕላዊ መግለጫ ያሳያል፡፡

፲፫. ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ጋር በመገናኘት ለሰበካው የሚያስፈልገውን ስታቲስቲካዊ መረጃ ሁሉ ይሰበስባል፡፡

## ምዕራፍ አምስት

## ስለ ወረዳ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ

### አንቀጽ ፴፩

### የወረዳ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ አመሠራረትና አ

፩. አመሠራረት፤

ሀ) በወረዳው ቤተ ክህነት ሥር ብዛታቸው ከአንድ ( አብያተ ክርስቲያናት በተወካዮቻቸው አማካይነት በወ ክህነት ሥራ አስኪያጅ ሊቀ መንበርነት በአንድነት የወረዳ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ያቋቁማሉ። ተወ ከእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ አስተ የተመረጡና በቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ የሚመሩ ኔ አንድ ምእመንና አንድ ወጣት ሲሆኑ የወረዳው ( ጸሐፊና የልዩ ልዩ ክፍል ኃላፊዎች አባላት ይሆና በዓመት አንድ ጊዜ የሚሰበሰብ የወረዳ ሰበካ ጠቅላ ጉባኤ ይሆናል።

ለ) የወረዳው ጠቅላላ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የተቋቋመ ከግቡ ለማድረስ ኃላፊነቱንና ተግባሩን ለማከናወን እን አንድ ጊዜ የሚሰበሰብ የወረዳ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ(ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) ይመርጣል።

፪. አቋም

በወረዳ ቤተ ክህነት ሥር፦

ሀ) የወረዳው ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ ሊቀ መን( አንድ ጠቅላላ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ( መላው የወ ክርስቲያናት ጠቅላላ ስብሰባ)፤

ለ) የወረዳ ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ ሊቀ መንበር የሆ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ(ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) እ ቤተ ክህነት አስተዳደር ጉባኤ፤

ሐ) የወረዳው ሰበካ አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት (የወረዳው ጽ/ቤት)፤

መ) የወረዳው ሰበካ ጉባኤ የሥራ ክፍሎች የወረዳው የሥራ ክፍሎች ናቸው።

---

### አንቀጽ ፴፪

### የወረዳ ጠቅላላ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ አባላት

፩. የወረዳ ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ ወይም እሱ በሌለበት ጊዜ በሀገረ ስብከቱ የተወከለ ካህን .................................... የጉባኤው ሊቀ መንበር፤

፪. በዚሁ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ ፫ እና ፬ ከተመለከቱት የካህናትና ምእ መናን ተወካዮች መካከል ዕድሜው ከ፴ ዓመት ያላነሰ ከ፸ ዓመት ያልበ ለጠ ብቁ ችሎታ ያለው በዚህ ጉባኤ የተመረጠ ካህን ወይም ምእመን .................................................................የጉባኤው ም/ሊቀ መንበር፤

፫. በወረዳ ክልል ውስጥ የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት አስተዳዳሪዎች ........................................................................የጉባኤው አባላት፤

፬. በወረዳ ክልል ውስጥ ከሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ተመርጠው የተወ ከሉ ካህናት ........................................................ የጉባኤው አባላት፤

፭. በወረዳው ክልል ውስጥ ከሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ተመርጠው የተወከሉ ምእመናን ................................................ የጉባኤው አባላት፤

፮. በወረዳው ክልል ውስጥ ከሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ተመርጠው የተወከሉ የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች ........................... የጉባኤው አባላት፤

፯. የወረዳው ቤተ ክህነት ጸሐፊ ወይም እሱ በሌለ ጊዜ በሀገረ ስብከቱ የተወ ከለ ካህን .............................................. የጉባኤው አባልና ጸሐፊ፤

### አንቀጽ ፴፫

### የወረዳ ጠቅላላ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር

በምዕራፍ ሁለት በአንቀጽ ፭ እና ፮ የተዘረዘረውን ዓላማና ተግባር እየፈጸመና እያስፈጸመ በተጨማሪ የወረዳ ጠቅላላ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ቀጥሎ የተመለከተው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል።

፩. በወረዳው ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ በኩል ተዘጋጅቶ በቀረበው የመነጋገሪያ አርእስት (አጀንዳ) መሠረት የወረዳውን ሰበካ አባላትና አገልጋዮች ሁኔታ፣ የሥራ ክንውን፣ የገንዘብና ንብረት አጠቃላይ መግለጫ ሰምቶ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፪. የቀረበለትን የወረዳውን ሰበካ የንብረት ሥራ እቅድና የልዩ ልዩ አገልግሎት መርሐ ግብር እየመረመረ ሲስማማበት ከአስተያየት ጋር ለመንበረ ጵጵስናው ሀገረ ስብከት መንፈሳዊ ጉባኤ ጽ/ቤት እንዲተላለፍ ያደርጋል፡፡

፫. ከበላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ቀርቦ ለተፈቀደው የሥራ እቅድና ልዩ ልዩ አገልግሎት የሚያስፈልገውን የገንዘብ መዋጮ ልክ ይወስናል፤ መሰብሰቡንና በሥራ ላይ መዋሉንም ይቆጣጠራል፡፡

፬. የወረዳውን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ገንዘብና ንብረት በሒሳብ አ (ኦዲተር) ያስመረምራል፡፡

፭. ለወረዳው ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ከአራት የማያንሱ ያልበለጡ አባላትን ይመርጣል፡፡

፮. በአስተዳደር ጉባኤ ተዘጋጅቶ የሚቀርብለትን የወረዳውን የውስ ደሪያ ደንብና ልዩ ልዩ መመሪያ መርምሮ ሲስማማበት ከአስተ ለሀገረ ስብከት ጽ/ቤት እንዲተላለፍ ያደርጋል፡፡

፯. የወረዳ ሰበካ ጠቅላላ መንፈሳዊ ጉባኤ ተጠሪነቱ ለመንበረ ጵጵ ስብከት ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ ፴፬

## የወረዳ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ

## (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) አባላት

፩. የወረዳው ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ ወይም እሱ በሌለበት ጊ ስ፦ነት የተወከለ ካህን ........................................ የጉባኤው ሰ

፪. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ ፫ እና፬ ከተመለከቱት የካህናት ምእመናን ተወካዮች መካከል ዕድሜው ከ፴ ዓመት ያላነሰ ከ፭ ያልበለጠ ብቁ ችሎታ ያለው በዚህ ጉባኤ የተመረጠ ካህን ወይ መን ........................................................የጉባኤው ም/ሊቀ

፫. ቁጥራቸው ከሁለት ያላነሱ ከአራት ያልበለጡ የአጥቢያ ቤተ ክ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤን የሚወክሉ ካህናት..................... የጉባኤ

፬. ከአንድ የወጣት ተወካይ ጋር ቁጥራቸው ከሁለት ያላነሱ ከአራ ያልበለጡ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤን የ ምእመናን......................................................................... የጉባኦ

፭. የወረዳው ቤተ ክህነት ጸሐፊ ወይም እሱ በሌለ ጊዜ በሀገረ ስ ከለ ካህን ........................................................ የጉባኤው አ

## አንቀጽ ፴፭

## የወረዳ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) ሥልጣንና ተግባ

በዚህ ቃለ ዓዋዲ በምዕራፍ ሁለት አንቀጽ ፭ እና ፮ ዓላማና ተግባር ሌላ በተጨማሪ የወረዳ ሰበካ መንፈሳዊ አስተ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡፡

፩.በወረዳው ውስጥ የሚገኙት የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ሰበካ ጉባኤያት የቆሙበትን ዓላማ ከግቡ እንዲያደርሱ ተግባራቸውንም እንዲያከናውኑ ያደርጋል፤ ይቆጣጠራል፡፡

፪. ከየአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የሚደርሱትን ልዩ ልዩ ጉዳዮችና መግለጫዎች መርምሮ አስፈላጊውንና ተገቢውን ተግባር ይፈጽማል፡፡

፫. ከየአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላላ አስተዳደርና ልዩ ልዩ አገልግሎት የሚከፈለውን ፳%(ሃያ ከመቶ) የገንዘብ አስተዋጽኦ ተቆጣጥሮ በወቅቱ ለሀገረ ስብከቱ ገቢ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

፬. በወረዳው ውስጥ ለጋራ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ጥቅም የሚውሉ የንብረት ሥራ እቅዶችንና የሰበካውን አገልግሎት መርሐ ግብር አዘጋጅቶ ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፡፡

፭. ለተፈቀደው የንብረት ሥራ እቀድ ማስፈጸሚያና ለልዩ ልዩ አገልግሎት ማከናወኛ ከእያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የተወሰነውን የገንዘብ መዋጮ በወረዳው ቤተ ክህነት ኃላፊነት በሕጋዊ ደረሰኝ እንዲሰበሰብ ያደርጋል፡፡

፮. እቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ ከሚመለከታቸው ጋር በአግባቡ ተባብሮ ይሠራል፤ ከበላይ የሚተላለፉትን መመሪያዎችና ትእዛዞች ይፈጽማል፤ ያስፈጽማል፡፡

፯. ለወረዳው ሰበካ አስተዳደር የሥራ መመሪያና የውስጥ ደንብ ከቃለ ዓዋ ዲው ጋር በማይቃረን ሁኔታ ተዘጋጅቶ በአንቀጽ ፴፫ ንዑስ አንቀጽ ፯ መሠረት ከታየ በኋላ ያለፈውን የሥራ ክንውን፣ የወደፊቱን ሥራ እቅድ፣ የበጀት ድልድልና እንዲሁም የሰበካውን አባላትና አገልጋዮች ሁኔታ መግለጫ ለወረዳው ጠቅላላ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ አቅርቦ ከታየና ስምም ነት ከተደረገበት በኋላ ለሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት እንዲተላለፍ ያደርጋል፡፡

፰. ከየአጥቢያው የሚቀርብለትን የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ፥ መመሪያና እቅድ ከዚህ ቃለ ዓዋዲና ከበላይ ከሚተላለፉት ድንጋጌዎች ጋር የማይቃ ረን መሆኑን መርምሮ ሲያረጋግጥ በወረዳው ሊቀ ካህናት በኩል ለሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ አቅርቦ እንዲጸድቅ ያደርጋል፡፡

፱. ከሰበካው መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ አባላት መካከል ለሀገረ ስብከቱ ጠቅላላ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የሚወከሉ ከወረዳው ቤተ ክህነት ሊቀ ካህናት ወይም ወኪል ሌላ አንድ ካህን፣ አንድ ምእመንና አንድ ወጣት ይመርጣል፡፡

፲. ለወረዳው ጠቅላላ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ከተወከሉት መካከል ለሀገረ ስብከቱ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ በመመረጣቸውና በሌላም ምክንያት የወረዳው ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ አባላት ቁጥር ከአምስት ያነሰ እንደሆን በምትካቸው በዚህ ቃለ ዓዋዲ በምዕራፍ ሦስት በአንቀጽ ፲፩ በንዑስ አንቀጽ ፩ በተገለጸው መሠረት ይፈጸማል፡፡

፲፪. የወረዳው ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ተጠሪነቱ ለወረዳው ጠቅላላ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ይሆናል፡፡

፲፫. የተመራጮች አባላት የአገልግሎት ዘመን በዚህ ቃለ ዓዋዲ ፲፩በንዑስ አንቀጽ ፪ በተገለጸው መሠረት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ ፴፮

## የወረዳ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት

፩. በወረዳው ክልል ውስጥ ለሚገኙት ገዳማት፥ አድባራትና የገጠ ክርስቲያናት እንዲሁም በየደረጃው ለተቋቋሙት ሰበካ መንፈ ጉባኤያት የሥራ አመራርና ከፍተኛ የአስተዳደር ኃላፊነት ያ መሥሪያ ቤት ነው፡፡

፪. ተጠሪነቱ ለሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ የሆነ የወረዳ ቤተ ክህነት አስኪያጅ ይኖራል፡፡

፫. የዚህን ቃለ ዓዋዲና ከሀገረ ስብከቱ የሚተላለፉትን ደንብና ሪ የሚፈጽምለትና የሚያስፈጽምለት አንድ የአስተዳደር ጉባኤና የሥራ ክፍሎችይኖሩታል፡፡

## አንቀጽ ፴፯

## የወረዳ ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና

በዚህ ቃለ ዓዋዲ በምዕራፍ ሁለት በአንቀጽ ፫ እና ፯ ዓላማና ተግባሩ እየፈጸመና እያስፈጸመ በተጨማሪ የወረዳው ሥራ አስኪያጅ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡፡

፩. የወረዳው ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ የወረዳው ጠቅላላ ሰበ ጉባኤና የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ሊቀ መንበርና የ አስፈጻሚ በመሆን በዚህ ቃለ ዓዋዲና ከበላይ በሚሰጠው መ መሠረት ሰበካ ጉባኤውን የመሰብሰብና በቃለ ጉባኤ የተመዘ ዎች የማስፈጸም እንደዚሁም የመጻጻፍ፣ የሒሳብና የንብረት ሌሎችንም የሰበካ ሥራዎችን የመሥራትና የማሠራት በጠቅላ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ አስተዳደር ኃላፊና ተጠሪ ነው፡፡

፪. በወረዳው ሰበካ ውስጥ የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት በሰበ አስተዳደር ጉባኤ በቃለ ዓዋዲው መሠረት እንዲደራጁና እን የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

፫. የወረዳው ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ ለአጥቢያ ቤተ ክርስተ መንፈሳዊ ጉባኤ ምርጫ አፈጻጸም ግንባር ቀደም አስተባባሪ ምርጫው ከመከናወኑ አስቀድሞ ለአጥቢያው ካህናትና ምእመ ዓዋዲውን የሚያጠናክር ትምህርት እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡

፬. በወረዳው የሚገኙትን የቤተ ክህነት ሠራተኞችንና ሌሎችንም ፈቃደኞችን በማስተባበር በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ አስተዳደርና ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች ውስጥ እንዲሳተፉ ያደርጋል፡፡

፭. ለወረዳው ቤተ ክህነት የሚያስፈልጉትን ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች ከሀገረ ስብከቱ መመሪያ እየተቀበለ ያቋቁማል፥ ያደራጃል፡፡

፮. ለየሰበካው ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚውሉትን የገንዘብና ንብረት ገቢና ወጪ ካርኒዎችንና ሞዴሎችን ሌሎችም አስፈላጊ እትሞችን ከሀገረ ስብከት ጽ/ቤት ጋር በመነጋገር በወቅቱ ያቀርባል ፣ ያከፋፍላል፡፡

፯. ማናቸውም የሰበካ አስተዳደርና የልዩ ልዩ ክፍሎች ሥራ በዚህ ቃለ ዓዋዲ መሠረት መካሄዱን ይቈጣጠራል፡፡

፰. በወረዳው ሰበካ ጉባኤ ውስጥ የሚገኙትን የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ(ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) አባላትና የሌሎችንም ኃላፊዎች ምርጫ እንዲጸድቅ ለሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ያቀርባል፡፡

፱. ከየአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ተዘጋጅቶ የሚቀርብለትንም የውስጥ ደንብ፣መመሪያና እቅድ ለወረዳው ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ አቅርቦ ካስጠና በኋላ እንዲጸድቅ ለሀገረ ስብከቱ ያስተላልፋል፤ ሲጸድቅም እንዲሠራበት ያደርጋል፡፡

፲. በየጊዜው የዕለትና የዘወትር መርሐ ግብር በማዘጋጀት በየሰበካው እየተዘዋወረ ወንጌልን በመስበክና በማሰበክ፣ ምእመናንን በማንቃትና በማትጋት የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ እንዲደራጅና እንዲጠናከር ያደርጋል፡፡

፲፩. በየጊዜው ከየአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ለሀገረ ስብከቱ የሚከፈለው የገንዘብ አስተዋጽኦ በወቅቱ መሰብሰቡንና ገቢ መሆኑን ይከታተላል፡፡

፲፪. ከየአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ተመዝግቦ ከቀረበለት መረጃ በተጨማሪ በልዩ ልዩ የትምህርትና የሥራ ተቋማት እንዲሁም በመሳሰሉት ድርጅቶች ሁሉ የሚገኙትን ካህናት፥ መምህራን፥ ሰባክያንና ምእመናን ከነቤተሰቦቻቸው እየመዘገበ የወረዳውን ስታቲስቲካዊ መረጃዎች፥ የበጀት ዓመቱን የሥራ ክንውንና የፋይናንስ ሪፖርት ለሀገረ ስብከቱ በወቅቱ ያቀርባል፡፡

# ምዕራፍ ስድስት

## ስለ መንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት መንፈሳዊ ጉባኤ

### አንቀጽ ፴፫

### የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት መንፈሳዊ ጉባኤ አመሠራረትና አቋም

፩. አመሠራረት፦

ሀ) በሀገረ ስብከት ሥር የሚገኙት በወረዳ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ(ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) የተመረጡ ከካህናት

አንድ፣ ከምእመናን አንድ ፣ ከሰንበት ት/ቤት ወ ከወረዳው ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ ጋር አራት እንዲሁም ከሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ ዋና የየክፍል ኃላፊዎች በአንድነት ተሰብስበው የመንበረ ስብከት ጠቅላላ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤን ይመሠርታ

ለ) በዚህ አኳኋን የተመሠረተው የመንበረ ጵጵስና ጠቅላላ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ በዓመት አንድ ጊ አንድ ጠቅላላ ጉባኤ ይኖረዋል፡፡

ሐ) ይህ የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ጠቅላላ ሰበካ መ ሥልጣኑንና ተግባሩን የሚያስፈጽምለት በየሦስት ወ የሚሰበሰብ የአስተዳደር ጉባኤ ወይም የሥራ አስ ይመርጣል፡፡

፪. አቋም፦

በመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ሥር፦

ሀ) የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ሊቀ መንበር የሆነበት ስብከት ጠቅላላ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ (የሀገረ ስ የቤተ ክርስቲያን ስብሰባ)፤

ለ) የሀገረ ስብከት መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (የሥ ኮሚቴ) እና የሀገረ ስብከቱ ቤተ ክህነት አስተዳደር

ሐ) የሰበካው ጉባኤ ጽ/ቤት (የሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት)፤

መ)የሰበካው ጉባኤ የሥራ ክፍሎች የሀገረ ስብከቱ ቤተ ክፍሎች ናቸው፡፡

### አንቀጽ ፴፬

### የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ጠቅላላ መንፈሳዊ ገ

፩. የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ................................ የጉባኤው

፪. ሊቀ ጳጳሱ በሌለበት ጊዜ የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ የጉ

........................................................................

፫. የሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት ዋና ጸሐፊና የክፍል ኃላፊዎች የጉ

፬. የወረዳዎች ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ ...................... የጉ

፭. በሀገረ ስብከቱ ውስጥ ከሚገኙት ወረዳ ሰበካ መንፈሳውያን የተወከሉ ካህናት ........................................................ የጉ

፮. በሀገረ ስብከቱ ውስጥ ከሚገኙት ወረዳ ሰበካ መንፈሳውያን የተወከሉ ምእመናን ................................................... የጉ

፯. በሀገረ ስብከቱ ውስጥ ከሚገኙት ወረዳ ሰበካ መንፈሳውያን የተወከሉ የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች ........................... የጉ

፰. ሊቀ ጳጳሱ የጉባኤው ሊቀ መንበር በሚሆንበት ጊዜ የሀገረ ካህናት (ሥራ አስኪያጅ) ................................ የጉባኤው

---

፱. የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ ሊቀ መንበር በሚሆንበት ጊዜ የሀገረ ስብከቱ ዋና ጸሐፊ......................................... የጉባኤው አባልና ጸሐፊ

### አንቀጽ ፴

### የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ጠቅላላ መንፈሳዊ ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር

በዚህ ቃለ ዓዋዲ በአንቀጽ ፭ እና ፮ የተመለከተውን ዓላማና ተግባር እየፈጸመና እያስፈጸመ በተጨማሪ የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ጠቅላላ መንፈሳዊ ጉባኤ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡፡

፩. ከቅዱስ ሲኖዶስ በየጊዜው የሚወጣውን ሕግና የዚህን ቃለ ዓዋዲ መሠረታዊ ሐሳብ ሳይለቅ ለሀገረ ስብከቱ መንፈሳዊ ጉባኤ የተዘጋጀውን የውስጥ መተዳደሪያ ደንብና የሥራ መመሪያ እንዲሁም ከአስተዳደር ጉባኤ የሚቀርቡለትን ልዩ ልዩ የሥራ እቅዶች አይቶ ከውሳኔ ሐሳብ ጋር ለሊቀ ጳጳሱ እንዲቀርብ ያደርጋል::

፪. በመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ(ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) ተቀናብሮ የቀረበውን የየአጥቢያውንና የየወረዳውን በጠቅላላው የክፍሉን ሀገረ ስብከት ያለፈውን የሥራ ክንውን የወደፊቱን የሥራ ዕቅድ የየሰበካውን ካህናትና ምእመናን ሁኔታ የገንዘብና ንብረት መግለጫ እየመረመረ በመነጋገሪያው አርእስት(አጀንዳ) መሠረት በየአንዳንዱ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ይሰጣል::

፫. የቤተ ክርስቲያንን የሥራ እንቅስቃሴ ለማጠናከር የመንፈሳዊ ት/ቤቶችን፣ የወንጌል መልእክተኞችን፣ የሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያትን፣ የልማት ሥራዎችን የበጎ አድራጎትና የማኅበራዊ አገልግሎቶችን በሀገረ ስብከቱ ውስጥ እንዲቋቋሙና እንዲስፋፉ ያደርጋል::

፬. በሀገረ ስብከት ደረጃ ለሚከናወኑት የሥራ እቅዶችና ልዩ ልዩ አገልግሎቶች የሚያስፈልገውን የገንዘብ መዋጮ ልክ ይወስናል፤ መሰብሰቡንና በሥራ ላይ መዋሉንም ያረጋግጣል::

፭. ከየአጥቢያው አብያተ ክርስቲያናት ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላላ አስተዳደርና ለልዩ ልዩ አገልግሎት የሚከፈለውን ፳% (ሃያ ከመቶ) የገንዘብ አስተዋጽኦ በወቅቱ ገቢ መሆኑን ይቆጣጠራል::

፮. በዚህ ቃለ ዓዋዲ በአንቀጽ ፵፩ ለተመለከቱት የአስተዳደር ጉባኤ አባላት የሚስማሙትን ከአራት የማያንሱ ከስምንት የማይበልጡ ካህናት፣ ምእመናንንና የሰንበት ት/ቤትን ወጣቶች ተወካይ በድምጽ ብልጫ ይመርጣል::

፯. የሀገረ ስብከት ጠቅላላ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ተጠሪነቱ ለመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ይሆናል::

## አንቀጽ ፵፩

## የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት መንፈሳዊ አስተዳ

## (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) አባላት

፩. የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ ........................ የጉባኤው

፪. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ ፫ እና ፬ ከተመለከቱት የካህና መናን ተወካዮች መካከል ዕድሜው ከ፴ ያላነሰ ከ፸ ዓመት ብቁ ችሎታ ያለው በዚህ ጉባኤ የተመረጠ ካህን ወይም ምእ ኤው .................................................................ም/ሰ

፫. ቁጥራቸው ከሁለት ያላነሱ ከአራት ያልበለጡ በሀገረ ስብከቱ መንፈሳዊ ጉባኤ የተመረጡ ካህናት ........................ የጉባ

፬. ከአንድ የወጣት ተወካይ ጋር ቁጥራቸው ከሁለት ያላነሱ ከአ ለጡ በሀገረ ስብከት ጠቅላላ መንፈሳዊ ጉባኤ የተመረጡ ምእ ................................................................ የጉባ

፭. የሀገረ ስብከቱ ዋና ጸሐፊ........................ የጉባኤው አ

## አንቀጽ ፵፪

## የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት መንፈሳዊ አስተዳ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) ሥልጣንና ተግባ

በዚህ ቃለ ዓዋዲ በአንቀጽ ፭ እና ፮ የተገለጸውን ዓ እየፈጸመና በትክክል መፈጸሙንም እየተቆጣጠረ የመንበረ ስብከት መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ የሚከተለው ሥልጣ ይኖረዋል::

፩. በቅዱስ ሲኖዶስ የወጣውን ሕግና ደንብ፥ በመንበረ ፓትርያ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የሚተላለፈውን ውሳኔና በመንበረ ጵጵ የሀገረ ስብከት መንፈሳዊ ጉባኤ የሚሰጠውን መመሪያ በሥራ ውል ያደርጋል::

፪. ስለ ስብከተ ወንጌል፣ ስለ መንፈሳዊ ትምህርት፣ ስለ ልማት ራጎት በጠቅላላው የሀገረ ስብከቱን ሀብትና አገልግሎት ለማስፋ እያወጣና ከየወረዳው የተላኩትን የሥራ እቅዶች እያጠና ከአ ለጠቅላላ ጉባኤው አቅርቦ ሲፈቀድ በሥራ ላይ እንዲውል ያ

፫. በጠቅላላው መንፈሳዊ ጉባኤ ውሳኔ መሠረት የተፈቀዱትን ጸጸም ይከታተላል::

፬. ለእቅዶቹ የተፈቀደው ገንዘብ በደንቡ መሠረት ወጭ ሆኖ ለ ሥራ መዋሉን ይቆጣጠራል::

፭. ከየአጥቢያው አብያተ ክርስቲያናት ከተሰበሰበው ፳% (ሃያ ከመቶ) እና ከማናቸውም የሀገረ ስብከቱ ገቢ ላይ ከዚህ በታች በተዘረዘረው መሠረት ለእያንዳንዱ እንደ ድርሻው እንዲከፈል ያደርጋል፡፡

ሀ) ለመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ....... ፴%

ለ) ለሀገረ ስብከቱ ........................................................ ፴%

ሐ) በሀገረ ስብከቱ ለሚገኙት የወረዳ ቤተ ክህነት ጽ/ቤቶች........ ፴%

መ) ለቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ................................ ፭%

ሠ) በሀገረ ስብከቱ ለሚገኙ የአብነት መምህራን......................... ፭%

፮. የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ከየአጥቢያው አብያተ ክርስቲያናት ከተሰበሰበው ፳% (ሃያ ከመቶ) እና ከማናቸውም የሀገረ ስብከቱ ገቢ ላይ ፦

ሀ) ለመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ፷፭% (ስድሳ አምስት ከመቶ)፣

ለ) ለሀገረ ስብከቱ ፴፭% (ሠላሳ አምስት ከመቶ) እንዲከፈል ያደርጋል፡፡

፯. የሀገረ ስብከቱን የልማትና ማኅበራዊ አገልግሎት ለማስፋፋት አግባብ ካላቸው ድርጅቶችና ባለሙያዎች ጋር በመተባበር የበጐ አድራጐትና ልዩ ልዩ የልማት ሥራዎችን ያከናውናል፡፡

፰. ከአጥቢያው አብያተ ክርስቲያናት ተዘጋጅቶ የሚቀርበውን ዓመታዊ የገንዘብ ድልድል (በጀት) አጥንቶ ከአስተያየት ጋር ለመንበረ ጵጵስናው ያቀርባል፡፡

፱. ማናቸውም የገንዘብ አስተዋጽኦ በወቅቱ መሰብሰቡንና እንዲሁም በደንቡ መሠረት በትክክል መያዙንና መጠበቁን ያረጋግጣል፡፡

፲. የሰበካውን አስተደደር፣ የገንዘብ አያያዝና የንብረት አጠባበቅ ይከታተላል፣ በየጊዜውም ገንዘቡንም ሆነ ንብረቱን በሒሳብ ተቆጣጣሪ ያስመረምራል፡፡

፲፩. ከየአጥቢያውና ከየወረዳው ተዘጋጅተው የሚቀርቡትን የውስጥ መተዳደሪያ ደንቦችና ልዩ ልዩ መመሪያዎች ከዚህ ቃለ ዓዋዲና ከበላይ ከሚመጡት ድንጋጌዎች ጋር የማይቃረኑ መሆናቸውን መርምሮ ሲያረጋግጥና ሊቀ ጳጳሱ ሲያጸድቅ እንዲሠራባቸው ያደርጋል፡፡

፲፪. በሀገረ ስብከቱ በየደረጃው የሚገኙት የሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያት ሁሉ የሰው ኃይላቸውን፣ የሥራ ክንውናቸውን፣ የወደፊት እቅዳቸውን፣ የንብረት ይዞታቸውን፣ የገንዘብ ገቢያቸውንና ወጪያቸውን በመግለጽ ሪፖርታቸውን አሟልተው በወቅቱ እንዲያቀርቡ በየጊዜው ማሳሰቢያና ማስታወቂያ ያስተላልፋል፡፡

፲፫. ለጠቅላላው ጉባኤ ስብሰባ ጠቅላላ መግለጫ፣ የመነጋገሪያ አርእስት (አጀንዳ)፣ የሥራ ፕሮግራም በቅድሚያ አዘጋጅቶ ያቀርባል፡፡

፲፬. የሰበካ መንፈሳዊ አስተደደር ጉባኤ(ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) እንደ አስፈላጊነቱ ጠቅላላ ጉባኤው እንዲጠራ ለጠቅላላ ጉባኤው ርእሰ መንበር (ሊቀ ጳጳስ)ያሳስባል፡፡

፲፭. ከሰበካው መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) አባላት መካከል በመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉ
የሚገኙ ከሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ ሌላ አንድ ካህን፣ አ
አንድ የሰንበት ት/ቤት ወጣት በድምሩ ሦስት ሰዎችን ይመ

፲፮. ከመንበረ ጵጵስናው ሀገረ ስብከት ጠቅላላ መንፈሳዊ አስተዳ
(ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) አባላት መካከል ለመንበረ ፓትርያ
ላይ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ፡በመመረጣቸውና በሌ
ያት የመንበረ ጵጵስናው ሀገረ ስብከት ሰበካ መንፈሳዊ አስተ
አባላት ብዛት ከአምስት ያነሰ እንደሆነ የመተካቱ ሥርዓት
ዓዋዲ ምዕራፍ ሦስት በአንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ ፬ በተገለ
መሠረት ይፈጽማል፡፡

፲፯. የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ጠቅላላ መንፈሳዊ አስተዳደ
አባላት የአገልግሎት ዘመን በዚህ ቃለ ዓዋዲ በምዕራፍ ሦስ
፲፩ በንዑስ አንቀጽ ፪ በተገለጸው መሠረት ይሆናል፡፡

፲፰. የሀገረ ስብከቱ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ(ሥራ አስፈጻሚ
ተጠሪነቱ ለመንበረ ጵጵስናው ሀገረ ስብከት ጠቅላላ መንፈሳ
ይሆናል፡፡

## አንቀጽ ፵፫

## የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት

፩. የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት በሀገረ ስብከቱ ክልል ለሚገኙት ገዳማት፥ አድባራትና የገጠር አብያተ ክርስቲያናት በየደረጃው ለተቋቋሙት ሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያትና ለወረዳ ክህነት የሥራ አመራርና ከፍተኛ የአስተዳደር ኃላፊነት ያለው ቤት ነው፡፡

፪. በሕገ ቤተ ክርስቲያን ድንጋጌ መሠረት እያንዳንዱ ሀገረ ስብ
በሊቀ ጳጳስ ወይም በጳጳስ፥ወይም በኤጲስ ቆጶስ ይመራል፡፡

፫. የሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት የዚህን ቃለ ዓዋዲ ዓላማና ተግባር እ
ከበላይ የሚተላለፈውን ሕግ፥ ደንብና መመሪያ የሚፈጸምበት

ጽምበት አንድ አስተዳደር ጉባኤና ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች ,

፬. አዲስ አበባ ሀገረ ስብከት በዚህ ቃለ ዓዋዲ ድንጋጌና ቅዱስ በሚያወጣው ልዩ ደንብና መመሪያ ይተደደራል።

## አንቀጽ ፵፬

## የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ሥልጣንና ተግባር

፩. ሊቀ ጳጳሱ የሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤትና ጠቅላላ የቤተ ክህነት አስተዳደር የበላይ ኃላፊ እንዲሁም የጠቅላላው ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ርእሰ መንበር ነው።

፪. በሀገረ ስብከቱ ለምትገኘው ለጠቅላላዋ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አባት እንደመሆኑ መጠን ለሰበካ ጉባኤያት መሪዎች በየጊዜው መንፈሳዊ ምክር፥መመሪያና ቡራኬ ይሰጣል፥ ያበረታታል፤ ለካህናት፤ ለምእመናን፥ ለሰንበት ት/ቤት ሕፃናትና ወጣቶች ትምህርት ይሰጣል፥ ያጽናናል።

፫. አንዲት፥ ቅድስት፥ ከሁሉ በላይና ሐዋርያዊት የሆነችው ቤተ ክርስቲያናችን ጥንታዊነትዋና ታሪካዊነትዋ በሰላም ተጠብቆ እንዲኖር እንዲሁም ተከታይዎችዋ ምእመናን በባእድ ሃይማኖት አስፋፊዎች እንዳይሰረቁ ብርቱ ጥበቃ ያደርጋል።

፬. በፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ ፮ እና ፯ በተደነገገው መሠረትና በዚህ ቃለ ዓዋዲ አንቀጽ ፳ ንዑስ አንቀጽ ፰ እና ፱ የተመለከተውን መስፈርት አሟልተው ለቀረቡት የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች በቃልና በጽሑፍ ፈተና እየተጣራ ፈተናውን ላለፉት ብቻ የዲቁናና የቅስና ማዕርግ ይሰጣል። ማዕርጉን ለተቀበሉትም የምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው ያደርጋል።

፭. ከሚያገለግሉበት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሸኛ ደብዳቤ ላልያዙና በቂ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ለሌላቸው ክህነት አይሰጥም።

፮. በሀገረ ስብከቱ አስተዳደር ጉባኤ እያስጠናና እያስወሰነ ለሀገረ ስብከቱ የሚያስፈልጉትን ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች እንዲቋቋሙና ኃላፊዎችም እንዲመደቡ ያደርጋል። አፈጻጸሙንም ለጠቅላይ ቤተ ክህነት ያሳውቃል።

፯. በሀገረ ስብከቱ ክልል ውስጥ አዲስ ለሚከተሉት አብያተ ክርስቲያናት በቀኖና ቤተ ክርስቲያን መሠረት ፈቃድ ይሰጣል፤ የመሠረት ድንጋይ ያኖራል፥ ቅዳሴ ቤቱን ይባርካል።

፰. በሀገረ ስብከቱ ክልል ውስጥ በመጀመሪያ ደረጃም ሆነ በይግባኝ የሚቀርበውን የሕግና ሥነ ሥርዓት ጉዳይ በሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት እንዲታይ ያደርጋል። ይግባኝ የሚጠየቅበት ጉዳይም ለጠቅላይ ቤተ ክህነት ወይም ለቅዱስ ሲኖዶስ እንዲተላለፍ ያደርጋል።

## አንቀጽ ፵፭

## የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር

፩. ሥራ አስኪያጁ በሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤትና በጠቅላላው የቤተ ክህነቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚና በሀገረ ስብከት ደረጃ የሰበካው መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ሊቀ መንበር ነው።

፪. ሊቀ ጳጳሱ በሌለበት ጊዜ ሥራ አስኪያጁ የሀገረ ስብከቱን (የ
ክህነቱን) አስተዳደር ጉባኤ በሊቀ መንበርነት ይመራል።

፫. ከቅዱስ ሲኖዶስ የሚወጣው መመሪያ ከመንበረ ፓትርያርክ
ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤና በሀገረ ስብከት ደረጃ የጠቅላላ ሰበካ
ጉባኤ ውሳኔዎች ለወረዳ ቤተ ክህነት ጽ/ቤቶችና ለአብያተ ክ
እንዲሁም በየደረጃው ለሚገኙት ሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያት
እንዲደርስ ያደርጋል፥ አፈጻጸሙንም ይከታተላል።

፬. በየጊዜው ከየአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን የሚከፈለውን የገንዘብ
ተቆጣጥሮ በወቅቱ ገቢ እንዲሆንና በአንቀጽ ፵፪ ንዑስ አንቀ
በተደነገገው መሠረት እንዲፈጸም ያደርጋል።

፭. ማናቸውም ወጪ ለሀገረ ስብከቱ በተፈቀደው በጀት መሠረት
እንደዚሁም የሒሳብ አያያዙና የንብረት አጠባበቁ በዚህ ቃለ
ከአንቀጽ ፳፭ እስከ ፳፯ በተደነገገው መሠረት መፈጸሙን ይ

፮. ለሰበካው መንፈሳውያን ጉባኤያት አገልግሎት የሚውሉትን የ
ካርኒዎች ሞዴሎች እንደዚሁም አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች እትሞ
በረ ፓትርያርኩ ጠቅላይ ጽ/ቤት የበላይ ተቆጣጣሪነትና በመ
ናው ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት ኃላፊነት አሳትሞ በወረዳው አማካ
ለአጥቢያ ሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያት ያከፋፍላል። በትክክ
ሉንም ይከታተላል።

፯. ሥራ አስኪያጁ ከሊቀ ጳጳሱ መመሪያ ሳይቀበል ሠራተኛ መ
ዝውውርን ደመወዝ መጨመርንና የመሳሰሉትን ሁሉ መፈጸም

፰. ከየወረዳው ቤተ ክህነት ተመዝግቦ ከቀረበለት መረጃ በተጨ
ልዩ የትምህርትና የሥራ ተቋማት እንዲሁም በመሳሰሉት ድር
የሚገኙትን ካህናት፥ መምህራን፥ ሰባክያንና ምእመናን ከነቤ
እየመዘገበ የሀገረ ስብከቱን ስታቲስቲካዊ መረጃዎች፥ የበጀት
የሥራ ክንውንና የፋይናንስ ሪፖርት ለሀገረ ስብከቱ በወቅቱ

፱. የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪነቱ ለሀገረ ስብከቱ ሊቀ

## ምዕራፍ ሰባት
## ስለ መንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈ(

### አንቀጽ ፴፩
### የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ
### አመሠራረትና አቋም

፩. አመሠራረት፦

ሀ) በመላው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክር
የእያንዳንዱ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጆች
ጽጽስናው ሰበካ አስተዳደር ጉባኤ ተመርጠ

የካህናት፣ የምእመናንና የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች በመንበረ ፓትርያርኩ ውስጥ ከቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ጋር እንዲሁም ከጠቅላይ ቤተ ክህነት የመምሪያና የድርጅት ኃላፊዎች ጋር በአንድነት ተሰብስበው የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤን ይመሠርታሉ::

ለ) በዚህ አኳኋን የተመሠረተው የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ በዓመት አንድ ጊዜ የሚሰበሰብ አንድ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ይኖረዋል፤ ይህም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አጠቃላይ ስብሰባ ይሆናል::

ሐ) ይኸው የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ሥልጣኑንና ተግባሩን የሚያስፈጽምለት በየአራት ወር አንድ ጊዜ የሚሰበሰብ የአስተዳደር ጉባኤ ወይም የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይመርጣል::

፪. አቋም፦

ሀ) ፓትርያርኩ ርእሰ መንበር የሆነበት አንድ የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ(የቤተ ክርስቲያን አጠቃላይ ስብሰባ)፤

ለ) የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ሊቀ መንበር የሆነበት አንድ የአስተዳደር ጉባኤ(ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) እና የጠቅላይ ቤተ ክህነት አስተዳደር ጉባኤ ፤

ሐ) የአጠቃላይ ሰበካ አስተዳደር ጽ/ቤት (የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት)፤

መ) የአጠቃላይ ሰበካ አስተዳደር የሥራ ክፍሎች የጠቅላይ ቤተ ክህነት መምሪያዎችና ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች ናቸው::

### አንቀጽ ፴፪

### የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ
### መንፈሳዊ ጉባኤ አባላት

፩. ፓትርያርኩ ..................................................... የጉባኤው ርእሰ መንበር
፪. ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ ................................ የጉባኤው ም/ሊቀ መንበር
፫. በየሀገረ ስብከቱና በቤተ ክርስቲያኒቱ ከፍተኛ ሥልጣን ላይ የተመደቡት ሊቃነ ጳጳሳት ..................................................... የጉባኤው አባላት
፬. የጠቅላይ ቤተ ክህነት ም/ሥራ አስኪያጅ ........ የጉባኤው አባልና ጸሐፊ
፭. የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ(ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) ..................................................... የጉባኤው አባላት
፮. የመንበረ ፓትርያርኩ ጠቅላይ ጽ/ቤት የኮሚሽን÷የየመምሪያውና የድርጅት ኃላፊዎች ..................................................... የጉባኤው አባላት
፯. የመንበረ ጽጽስና ሀገረ ስብከት ሊቃነ ካህናት(ሥራ አስኪያ( ..................................................... የገ
፰. ከየመንበረ ጽጽስና ሀገረ ስብከት መንፈሳውያን አስተዳደር ተመርጠው የተወከሉ ካህናት ........................................ የጉ
፱. ከየመንበረ ጽጽስና ሀገረ ስብከት መንፈሳውያን አስተዳደር ተመርጠው የተወከሉ ምእመናን........................................ የጉ
፲. ከየመንበረ ጽጽስና ሀገረ ስብከት ሰበካ መንፈሳውያን አስተ( ተመርጠው የተወከሉ የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች ......... የገ
፲፩. በውጭ ሀገር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲ ..................................................... የገ

## አንቀጽ ፴፰

## የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር

በዚህ ቃለ ዓዋዲ አንቀጽ ፭ እና ፮ የተዘረዘሩትን '
እየፈጸመና እያስፈጸመ በተጨማሪ የመንበረ ፓትርያርኩ ›
መንፈሳዊ ጉባኤ ቀጥሎ የተመለከተው ሥልጣንና ተግባር ይኖ

፩. የየሀገረ ስብከቱን መግለጫዎች እንዲሁም የወደፊት እቅዶች
በቅድሚያ በተዘጋጀው የመነጋገሪያ አርእስት(አጀንዳ) መሠ
በአንድ በጉዳዩ ላይ ተወያይቶና ተመካክሮ ይወስናል::
፪. በአጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ(ሥራ አስፈጻ
በኩል ተጣርተው የሚቀርቡትን የየሀገረ ስብከት ከፍተኛ የሰ
ጉዳዮችን እየመረመረ አስፈላጊውንና ተገቢውን ይፈጽማል::
፫. የቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት ለማ
የመንፈሳዊ ት/ቤቶች፣ የካህናት፣ የሰባክያንና የሰንበት ት/
ማሠልጠኛዎች፣ የልማትና በጎ አድራጎት ተቋሞች በሀገረ
በማዕከል ደረጃ እንዲቋቋሙና እንዲደራጁ ያደርጋል::
፬. በዚህ ቃለ ዓዋዲ በአንቀጽ ፴፱ የተዘረዘሩትን ከአራት ያላነ
ያልበለጡ የአጠቃላዩን አስተዳደር ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ(ሥ
ኮሚቴ) አባላት ይመርጣል::
፭. የተመረጡት አባላት የአገልግሎት ዘመን በዚህ ቃለ ዓዋዲ
ሦስት በአንቀጽ ፲፩ በንዑስ አንቀጽ ፪ በተገለጸው መሠረት
፮. የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ተጠ
ሲኖዶስ ነው::

## አንቀጽ ፴፱

## የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ(ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) አባላት

፩. የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ... የጉባኤው ሊቀ መንበር
፪. የጠቅላይ ቤተ ክህነት ም/ሥራ አስኪያጅ የጉባኤው ....................................................................አንደኛ ም/ሊቀ መንበር
፫. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ ፬ እና ፭ ከተመለከቱት የካህናትና የምእመናን ተወካዮች መካከል ዕድሜው ከ፴ ያላነሰ ከ፸ ዓመት ያልበለጠ ብቁ ችሎታ ያለው በዚህ ጉባኤ የተመረጠ ካህን ወይም ምእመን ....................................................የጉባኤው ሁለተኛ ም/ሊቀ መንበር
፬. ቁጥራቸው ከሁለት ያላነሱ ከአራት ያልበለጡ በአጠቃላይ ጉባኤው ተመርጠው የተወከሉ ካህናት ........................................ የጉባኤው አባላት፤
፭. ከአንድ የወጣት ተወካይ ጋር ቁጥራቸው ከሁለት ያላነሱ ከአራት ያልበለጡ በአጠቃላይ ጉባኤው ተመርጠው የተወከሉ ምእምናን ........................................................................ የጉባኤው አባላት፤
፮. የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ሰበካ ጉባኤ መምሪያ ኃላፊ ........................................................................የጉባኤው አባል፤
፯. የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ሰበካ ጉባኤ መምሪያ ዋና ጸሐፊ ........................................................................ የጉባኤው ጸሐፊ

## አንቀጽ ፵

## የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ(ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) ሥልጣንና ተግባር

በዚህ ቃለ ዓዋዲ በአንቀጽ ፭ እና ፮ የተዘረዘሩትን የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ዓላማና ተግባር እየፈጸመና በሥራ መተርጐሙን እየተቆጣጠረ በተጨማሪ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል::

፩. በቅዱስ ሲኖዶስ የሚወጣውን ደንብና መመሪያ እንዲሁም በመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የሚተላለፈውን ውሳኔና መግለጫ ለየሀገረ ስብከቱና ለሚመለከታቸው ሁሉ በወቅቱ እንዲደርሳቸው ያደርጋል፤ ተግባራዊ መሆኑንም ይከታተላል::
፪. በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሚሠሩት ከፍተኛ እቅዶችና ለልዩ ልዩ መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት የተወሰነውን የገንዘብ መዋጮ በደንቡ መሠረት በትክክል መያዙንና መጠበቁን ይከታተላል::

፫. ከየአጥቢያው አብያተ ክርስቲያናት ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተ ክርስቲያን ጠቅላላ አስተዳደርና ለልዩ ልዩ አገልግሎት የሚከ የገንዘብ አስተዋጽኦ ተቆጣጥሮ በየጊዜው ገቢ መሆኑንና አለመ ያረጋግጣል፡፡

፬. የአጠቃላዩ ሰበካ አስተዳደር ገንዘብ አያያዝና የንብረት አጠባ ቃለ ዓዋዲ ከአንቀጽ ፳፭ እስከ ፳፯ በተደነገገው መሠረት ơ ይከታተላል፤ በሒሳብ አጣሪም ያስመረምራል፡፡

፭. የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የመተዳደሪያ ደንብና የሥራ መመሪ ዚሁም ሊሻሻል የሚገባውን የሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያት ሕ ልዩ ድንጋጌዎች እያጠና ለአጠቃላዩ ጉባኤ ያቀርባል፡፡

፮. በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሚከናወኑት የቤተ ክርስቲያን ዓይነተኛ ማለት ስለ ስብከተ ወንጌል ፥ ስለ መንፈሳዊ ትምህርት፣ ስለ ስለ በጐ አድራጐትና ስለ መሳሰሉት እንደዚሁም ስለ ሰበካ ጉባኤያት ሀብትና አገልግሎት መስፋፋት ጉዳይ እቅድ እያወ ግብር እያዘጋጀ ለአጠቃላዩ ጉባኤ አቅርቦ ሲፈቀድለት በሥራ እንዲውል ያደርጋል፡፡

፯. ለመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ስብሰባ አጠ ሪፖርትና ልዩ ልዩ መግለጫዎች፣ ለጉባኤው የመነጋገሪያ አር (አጀንዳ) እና መርሐ ግብር ያዘጋጃል፡፡

፰. የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ወይም ሥራ አስፈጻሚ ኮ ተጠሪነቱ ለመንበረ ፓትርያርኩ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባ

## አንቀጽ ፶፩

## የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ

፩. በሀገር ውስጥና በውጭ ለሚገኙት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋ ክርስቲያን መንበረ ጵጵስና አህጉረ ስብከት፥ ለገዳማትና አድባ ሁም በየደረጃው ለተቋቋሙት ሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያት ເ ዳደር ማዕከልና ርእስ፣ ለቤተ ክህነት ሥራ አመራርና ለመንፈ አገልግሎት ሁሉ የበላይ ኃላፊና ባለሙሉ ሥልጣን መሥሪያ

፪. የቅዱስ ሲኖዶስ ሕግና ደንብ ፥ የቋሚ ሲኖዶስ ውሳኔና መመ ሁም የቃለ ዓዋዲው ድንጋጌ ሁሉ ተግባራዊ የሚሆነው በጽ/ቤ በሚገኙት መምሪያዎችና ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች አማካይነት

፫. ከየሀገረ ስብከቱ የሚቀርቡትን የአስተዳደርና የፍትሕ መንፈሳ እየተቀበለ የሚወስን አንድ የአስተዳደር ጉባኤ አለው፡፡

## አንቀጽ ፶፪

## የፓትርያርክ ሥልጣንና ተግባር

፩. ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ለመላዋ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የበላይ ጠባቂ፥ ለአንድነትዋና ለአስተዳደርዋ ከፍተኛ ኃላፊና ባለሙሉ ሥልጣን በመሆኑ የቅዱስ ሲኖዶስንና የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤን በርእሰ መንበርነት ይመራል፡፡

፪. ፓትርያርኩ የሁሉም መንፈሳዊ አባትና መሪ እንደ መሆኑ መጠን በየደ ረጃው ለሚገኙት የሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያት መሪዎች እንዲሁም ለካህ ናትና ለምእመናን መመሪያ፣ ትምህርትና ቡራኬ ይሰጣል፡፡

፫. በመጀመሪያ ደረጃም ሆነ በይግባኝ የሚቀርቡት ጉዳዮች በጠቅላይ ቤተ ክህነት ወይም በቋሚ ሲኖዶስ ወይም በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ እንዲታዩና ውሳኔ እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

፬. ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖትን የሚያፋልሱና ሌሎችም የቤተ ክርስ ቲያን ዓበይት ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ለመላው የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት(ሊቃነ ጳጳሳት)፣ አስፈላጊም ከሆነ ለመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈ ሳዊ ጉባኤ አባላት አስቸኳይ ጥሪ የማድረግ መብትና ኃላፊነት አለው፡፡

፭. ከጥንት ጀምሮ ያለው የአኃት ኦሪየንታል ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት መንፈሳዊና ማኅበራዊ ግንኙነት በበለጠ እንዲስፋፋና እንዲጠ ናከር ያደርጋል፡፡

## አንቀጽ ፶፫

## የጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ ሥልጣንና ተግባር

፩. ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ ለመላዋ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሥራ አመራር፣ የገንዘብና ንብረት አስተዳደር የበላይ ኃላፊ በጠቅላላው የቤተ ክህነት ዋና ባለሥልጣን ነው፡፡
፪. ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤን በም/ሊቀ መንበርነት፣ የጠቅላይ ቤተ ክህነት አስተዳደር ጉባኤንና የአጠቃላዩን ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤን በዋና ሊቀ መንበርነት ይመራል፡፡
፫. የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የቆመለትን ዓላማና ተግባር ለመፈጸምና ልዩ ልዩ የክፍል ሥራዎችንም ለማሟላት የጠቅላይ ቤተ ክህነት መምሪያዎች ስለ ስብከተ ወንጌል፣ ስለቋሚ መንፈሳዊ ት/ቤትና ስለ ሰንበት ት/ቤት መስ ፋፋትና መጠናከር፣ ስለ ሰበካ ጉባኤ አስተዳደርና ስለ ካህናት አገልግሎት መሻሻል፣ ስለ ሥነ ጽሑፍ ዝግጅትና ስርጭት፣ ስለ ቅርሶችና ስለ ንዋየ

ቅድሳት አጠባበቅ የሥራ መመሪያ ይሰጣል፤ እያንዳንዱ የ ኃላፊም የተመደበበትን የሥራ ድርሻ በትክክል እያከናወነ መ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡
፬. በመጀመሪያ ደረጃም ሆነ በይግባኝ የሚቀርቡትን ጉዳዮች በ ርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት አስተዳደር ጉባኤ እንዲታዩና እን ያደርጋል፤ ከዚህ ጉባኤ ሥልጣን በላይ የሆነውን ጉዳይ ለቋሚ ወይም ለቅዱስ ሲኖዶስ ያቀርባል፡፡
፭. በየጊዜው ከየሰበካው ቤተ ክርስቲያን ለጠቅላላው አገልግሎት ተብሎ የሚከፈለው የገንዘብ አስተዋጽኦ ተጠቃልሎ መሰብሰቡ ለኛው ቦታ በወቅቱ ገቢ መሆኑን ይከታተላል፡፡
፮. ማናቸውም ዓይነት ወጪ በሚደረግበት ጊዜ ለመንበረ ፓትር ቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ በተፈቀደው በጀት መሠረት መ እንደዚሁም የሒሳቡ አያያዝና የንብረቱ አጠባበቅ በዚህ ቃለ አንቀጽ ፳፫፣፳፮፣፳፯ እና፶፮ በተዘረዘረው መሠረት መፈጸ ይቆጣጠራል፡፡
፯. በበጀት የተመደበውን ማንኛውንም የቤተ ክርስቲያኒቱን ገንዘ በፊርማው ያንቀሳቅሳል፡፡ በየዓመቱና አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት በሕጋዊ ኦዲተር እንዲመረመር ያደርጋል፡፡
፰. በውጭ ሀገር የሚገኙትን አህጉረ ስብከትና አብያተ ክርስቲያ ሂደታቸውን ይከታተላል ፥ ይቆጣጠራል፡፡
፱. የየዓመቱን የሥራ ፍሬና የወደፊቱንም ዕቅድ የሚያስረዳ ሪፖ በየዓመቱ በጥቅምት ወር ለሚደረገው አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳ ያቀርባል፤ አጠቃላይ ጉባኤው የመከረበትና ያሳለፈው የውሳኔ ለቅዱስ ሲኖዶስ ቀርቦ ሲጸድቅ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋ

## አንቀጽ ፶፬

## ስለ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ም/ሥራ አስኪያ

፩. ም/ሥራ አስኪያጁ
 ሀ) ከጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ በመመሪያ ተለይተው ተግባራት ያከናውናል፤
 ለ) ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶት ይ
፪. ም/ሥራ አስኪያጁ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ ይሆና

# ምዕራፍ ስምንት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ ፶፩

### የሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያት የአመራር ሥነ ሥርዓትና ተጨማሪ የስብሰባ ጊዜ

፩. የሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያት አመራር ሥነ ሥርዓት፤

በየደረጃው የሚገኙት የሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያት የአመራር ሥነ ሥርዓት ቀጥሎ እንደተመለከተው ይሆናል፡፡

ሀ) በማናቸውም ደረጃ የሚገኝ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ከአባሎቹ ከሦስቱ ሁለት እጅ ከተገኙ ጉባኤው እንደ ሞላ ተቆጥሮ ሥራውን ሊቀጥል ይችላል፡፡

ለ) ለጉባኤው የቀረቡት ጉዳዮች የሚወሰኑት በዕለቱ በተገኙት አባሎች ድምጽ ብልጫ ሲሆን ድምፁ እኩል በእኩል በሚሆንበት ጊዜ ሊቀ መንበሩ ያለበት ወገን ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፡፡

ሐ) በእያንዳንዱ ስብሰባ ላይ የተወሰነው ጉዳይ በቃለ ጉባኤ ተዘጋጅቶ በዕለቱ ስብሰባ ላይ የተገኙ አባላት በሙሉ ይፈርሙበታል፡፡

መ) የሰበካውን መንፈሳዊ ጉባኤ ውሳኔ የመፈጸምና የማስፈጸም ኃላፊነት የጉባኤው ሊቀ መንበር ነው፡፡

፪. ተጨማሪ የስብሰባ ጊዜ

በዚህ ቃለ ዓዋዲ በምዕራፍ ሦስት በአንቀጽ ፯ በንዑስ አንቀጽ ፩ በፊደል (ለ) እና (ሐ) በምዕራፍ አምስት አንቀጽ ፴፩ ንዑስ አንቀጽ ፩ በምዕራፍ ስድስት አንቀጽ ፴፯ ንዑስ አንቀጽ ፩ በፊደል (ለ) እና (ሐ) በምዕራፍ ሰባት አንቀጽ ፵፩ ንዑስ አንቀጽ ፩ በፊደል (ለ) እና (ሐ) ከተገለጸው መደበኛ የስብሰባ ጊዜ በተጨማሪ በየደረጃው የሚገኙት ሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤት አስቸኳይ ጉዳይ ሲገጥማቸውና አስፈላጊ የሆነ ምክንያት ሲኖራቸው ወይም ከጉባኤው አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሆኑት ስብሰባ እንዲደረግ ሲጠይቁ በየሊቃነ መናብርቶቻቸው ጥሪ በማናቸውም ጊዜ ስብሰባ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

### አንቀጽ ፶፪

### ስለ ሰበካው ቤተ ክርስቲያን ልዩ ልዩ ገቢ

በቅዱሳት መጻሕፍት በኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ ፳፯ እስከ ፴፫፤ በኦሪት ዘዳግም ምዕራፍ ፲፬ ከቁጥር ፳፪ እስከ ዘኍልቍ ምዕራፍ ፲፰ ከቁጥር ፳ እስከ ፳፰ ነህምያ ምዕ. ሚል. ምዕ. ፫፥፯-፲፫፤ ማቴዎስ ምዕራፍ ፳፪ ቁጥር ፳፩፤ ሥራ ምዕራፍ ፬ ቁጥር ፴፪-፴፯፤ ፩ኛ ቆሮንቶስ ምዕ.፲፯ ከቁ ፯ እንደተደነገገው ማንኛውም ምእመን ከሚያገኘው ከማናቸው ንብረቱ ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ አገልግሎትና ለቤተ አገልጋዮች ካህናት በጠቅላላው ለመንፈሳዊና ማኅበራዊ የሚውል አሥራት በኩራት መክፈል ክርስቲያናዊ ግዴታው ነው፡

ከሰበካው ካህናትና ምእመናንም ሆነ ከሌሎች ልዩ ልዩ በ… የቤተ ክርስቲያን የገቢ ዓይነት ቀጥሎ የተመለከተው ነው፡፡

፩. የወርና የዓመት አስተዋጽኦ፤

ሀ) ገቢ ያለው ካህንም ሆነ ምእመን ለሰበካው ቤተ አስተዋጽኦ (አሥራት) በወር ከአንድ ብር እስከ ሁ… በዓመት ከአሥራ ሁለት ብር እስከ ሃያ አራት ብር …

ለ) በጐ ፈቃድ ያለው ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው የበለጠ ሊያደርግ ይችላል፡፡

ሐ) ጥሬ ገንዘብ መክፈል ያልቻለ በዓይነት ከምር… አስተዋጽኦ ማድረግ ክርስቲያናዊ ግዴታው ነው፡፡

መ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከፊደል (ሀ) እስከ (ሐ) የተ… አስተዋጽኦ መክፈል የማይችል ቢኖር ሁኔታው… መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ(ሥራ አስፈጻሚ ኮሚ… ሊከፍል በሚችለው መጠን ይወሰንለታል፡፡ ፈጽሞ የማይችል ከሆነም በነፃ መንፈሳዊ አገልግሎት ይፈጸም…

ሠ) በጉልበትና በአእምሮ ሥራ መርዳት የሚችል እንደችሎታው ለቤተ ክርስቲያን ተገቢውን አገልግሎ… አለበት፡፡

፪. <u>ከሰበካውና ከሌሎች ምእመናን የሚገኘው የገንዘብ ገቢ፣</u>

ሀ) ስእለት

ለ) ሙዳየ ምጽዋት

ሐ) ስጦታ(መባዕ)

መ) የወርና የዓመት በዓል ርዳታ

ሠ) የቅርጻ ቅርጽና የተግባረ ዕድ ሽያጭ

ረ) ከጠበል አገልግሎትና ከቤተ ክርስቲያን ጐብኝዎች

ሰ) ከሰንበት ት/ቤት መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎቶች

ሸ) ከልዩ ልዩ የልማት ሥራዎች

ቀ) በዚህ የገቢ አርእስት ውስጥ ያልተጠቀሰ ማናቸውም ዓይነት ገቢና ሌላም ልዩ ልዩ የገቢ ምንጮችን በመፍጠር የሚገኝ ገንዘብና ንብረት ይሆናል::

፫. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ በዝርዝር የተገለጸው ገንዘብና ንብረት ተጠቃልሎ በቤተ ክርስቲያኑ ግምጃ ቤት በሰበካው ገንዘብ ቤት ገቢ ይሆናል::

፬. ማናቸውም ዓይነት የሰበካው ገንዘብና ንብረት ገቢ ለቁጥጥር እንዲያመች በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት የበላይ ተቆጣጣሪነትና በመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት ኃላፊነት ታትሞ በሚወጣው በአንድ ዓይነት ሕጋዊ ደረሰኝ (ካርኒ) ብቻ ይሰበሰባል::

፭. ይህንን ቃለ ዓዋዲ በመተላለፍ የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት ሳያውቀውና ሳይፈቅድ በሰበካው ቤተ ክርስቲያን ስም ሌላ የገቢ ካርኒ አሳትሞ የሚሠራ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ወይም ግለሰብ ተጠያቂ ይሆናል፤ ሲሠራባቸው የተገኙ ካርኒዎችም ዋጋ እንደሌላቸው ተቆጥሮ እንዳይሠራባቸው ይታሸጋሉ:: በተያዙት ካርኒዎች የተሰበሰበው ገንዘብም በሕጋዊ ደረሰኝ ለቤተ ክርስቲያኑ ገቢ ይሆናል::

፮. በየአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የሚገኘው ገንዘብ በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ስም፣ ከወረዳ እስከ መንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የሚገኘው ገንዘብ በየደረጃው በተቋቋ መው የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ስም የባንክ ሒሳብ ተከፍቶለት ይቀመጣል::

## <u>አንቀጽ ፵፯</u>

## <u>ስለ ሰበካው ቤተ ክርስቲያን ልዩ ልዩ ወጪ</u>

የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የገንዘብ ወጪ ከዚህ ቀጥሎ እንደተመለከተው ይሆናል::

፩. አጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ከካህናትና ከምእመናን አስተወጽኦ፣ ከስእለት፣ ከሙዳየ ምጽዋት፣ ከልማት ሥራዎችና ከማናቸውም ገቢ ላይ ፳% (ሃያ ከመቶ) ለሀገረ ስብከት ይከፍላል:: ሀገረ ስብከቱም በዚህ ቃለ ዓዋዲ አንቀጽ ፵፪ ንዑስ አንቀጽ ፭ መሠረት ክፍያውን ይፈጽማል::

፪. ከበላይ አካል በተፈቀደ በጀት ድልድል መሠረት፦

ሀ) ለደሞዝ

ለ) ለሥራ ማስኪያጃ

ሐ) በእቅድ ለተያዙ ልዩ ልዩ ሥራዎች ወጪ ያደርጋል::

፫. ከቤተ ክርስቲያኒቱ ወይም በየደረጃው ከሚገኘው የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ገንዘብ ቤት ወይም ግምጃ ቤት የገንዘብ ወጭ የሚደረገው በተፈቀደው ዓመታዊ የገንዘብ ድልድል (በጀት) መሠረት የሰበካው ሊቀ መንበር በጽሑፍ ሲያዝ ብቻ ነው::

፬. በማናቸውም ደረጃ የሚገኘው የሰበካ አስተዳደር የበጀት ዓመ ቀን ተጀምሮ ሰኔ ፴ ቀን ይዘጋል::

፭. በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በየደረጃው የተጠናቀረው የንብረት አጠባበቅ የገንዘብ ገቢና ወጭ ሒሳብና የሥራ ክንውን ሪፖር ሐምሌ ፴ ቀን ድረስ መንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ጽ/ቤ አለበት፤ ሀገረ ስብከት ጽ/ቤትም የበኩሉን አጥንቶና አጣርቶ ሪፖርት እስከ ነሐሴ ፴ ቀን መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጸ ደርስ ያደርጋል::

፮. በየደረጃው የተቋቋሙት ሰበካ ጉባኤያት ከተፈቀደላቸው በጀት ዘብ ወጭ ማድረግ አይችሉም::

፯. የእያንዳንዱ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ገቢ የአንዱ ዓመት ከፍ ዓመት ገቢ ዝቅ ሊል ስለሚችል ለደመወዝ፣ ለሥራ ማስኪያጃ ክርስቲያን ማደሻ ታጥቶ ችግር እንዳይደርስ አስቀድሞ ጥንቃ ማናቸውም የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ጽ/ቤት አዲስ የበጀት ድል በሚያደርግበት ወቅት በበጀት ከሚደለደለው ሒሳብ ላይ ለመለ የሚሆን ገንዘብ በተካባችነት በባንክ ማስቀመጥ አለበት፤ ይህም የሚንቀሳቀሰው ተጠንቶ ሲቀርብ በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ፈቃ ይሆናል::

## አንቀጽ ፻፫

## የንብረትና ታሪካዊ ቅርሶች አመዘጋገብና አያ

፩. በቤተ ክርስቲያን ስም የሚገኙት ንዋያተ ቅድሳትና ጥንታውያ አመዘጋገብ በቤተ ክርስቲያኒቱ ቋንቋ የግዕዝ ፊደልና አሐዝ እ የተለመደው የመለያ ቁጥር(ኮድ) እየተሰጣቸው በቀዋሚ ባሕር ተመዝግበው በጥንቃቄ ይቀመጣሉ።

፪. በየገዳማት፣ አድባራትና ገጠር አብያተ ክርስቲያናት የሚገኙት ውያን የሆኑት ቅርሶች በተፈጥሮና በሰው ሠራሽ ችግር ምክንያ የሚደርስባቸው መሆኑ ሲታመንበት ከሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ትእዛዝ እንዲንቀሳቀሱ ካልተደረገ ካሉበት ታሪካዊ ቦታ በምንም ዓይነት መንቀሳቀስ የለባቸውም

፫. የአንዱን ቤተ ክርስቲያን ቅርስ ወይም ንብረት ካለበት ቦታ ያዛወረ ወይም የሰወረ ወይም የሠረቀና ያሠረቀ ወይም የሸጠና ግለሰብ ወይም ድርጅት ቢኖር በፈጸመው ወንጀል ተጠያቂ ከ አድራጐቱን የፈጸመው ሰው ካህን ከሆነ ከሥልጣነ ክህነቱ፥ ከ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎትና ከጥቅሙ ሁሉ ታግዶ በሀገረ ስ ጳጳስ ወይም በሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት አማካኝነት ለቅዱስ ሲኖዶ አስፈላጊው ቅጣት ይወሰንበታል።

## አንቀጽ ፻፬

## ስለሚሾሙ፣ ስለሚቀጠሩና በበጐ ፈቃድ ቤተ ክርስቲያንን ስለሚያገለግሉ

፩. በሙያቸው ብቁ የሆኑ ከትዕቢት፥ ከትንኮል፥ ከአድማ፥ ከስካርና ከልዩ ልዩ አስነዋሪ ነገሮች የራቁ ፣ በመልካም ሥነ ምግባራቸውና በመንፈሳዊነታቸው የተመሰከረላቸው ከካህናት መካከል እየተመረጡ፦

ሀ) የታላላቅ ገዳማትና አድባራት አስተዳዳሪዎች በሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ አቅራቢነት በቅዱስ ፓትርያርክ ይሾማሉ።

ለ) የንዑሳን ገዳማትና አድባራት እንዲሁም የገጠር አብያተ ክርስቲያናት አስተዳዳሪዎችና ሊቀ ጠበብቶች በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ፊቃድና ፊርማ ይሾማሉ።

፪. ከዚህ በላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በአንድነት በመቁነን የሚተዳደሩ የወንድ ወይም የሴት ገዳማት መነኮሳት ወይም መነኮሳይያት በሥርዓተ ገዳሙ መሠረት አበምኔታቸውን ወይም እመምኔታቸውን መርጠው ሲአቀርቡ በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ይጸድቃል።

፫. ቄሰ ገበዝ፣ መሪጌታ፣ ቀኝጌታ፣ ግራጌታ፣ ርእሰ ደብር፣ አጋፋሪና ሊቀ ዲያቆናት በመባል የሚሰጡት የቤተ ክርስቲያን ማዕርጋተ ሢመት ሙያቸውና ሥነ ምግባራቸው በካህናት ጉባኤ እየተጠና የሚመረጡት ካህናት በቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ለሊቀ ጳጳሱ ቀርቦ ሲስማማበት በአስተዳዳሪው ይሾማሉ።

፬. የአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ከሀገረ ስብከት በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የጠባይና የሥራ ችሎታ (የሙያ) መመዘኛ ሥራውንና ቦታውን በመጥቀስ በይፋ ማስታወቂያ አውጥቶ በማወዳደር መምህራንን፣ ሰባክያንን፣ ቀሳውስትን፣ ዲያቆናትን፣ መዘምራንንና ልዩ ልዩ ሠራተኞችን ሊቀጥር የሚችለው በወረዳው ቤተ ክህነት ኃላፊነት ይሆናል። ይህም ቅጥር በሥራ ላይ የሚውለው የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ሲያጸድቀው ነው።

፭. በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ቅዱስ ሲኖዶስ በሚያወጣው ደንብ መሠረት በሀገረ ስብከቱ በኩል በፈተና ተወዳድረው የሚያልፉት ብቻ ከሚላኩላቸው በስተቀር በአጥቢያው አስተዳዳሪ ወይም በሰበካ ጉባኤ ሥልጣን ማንኛውም ቅጥር ሊፈጸም አይችልም።

፮. ከመንበረ ፓትርያርክ እስከ ወረዳ ቤተ ክህነት የሚመደቡት ሠራተኞች የቅጥር ሁኔታ ግን በማዕከል ደረጃ በጠቅላይ ቤተ ክህነት እንደ ሥራው አስፈላጊነት እየተጠና ይፈጸማል።

፯. የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በካህናትና በምእመናን ኅብረት የተመሠረተ እንደ መሆኑ መጠን ደመወዝ ከሚያገኙትና በቋሚነት ከተመደቡት ካህናት ውጭ የሌሎችን እውቀትና ጉልበት መጨመር(ማግኘት) እንዲቻል።

ሀ) በየመሥሪያ ቤቱ በሥራ ላይ የሚገኙ ካህናት በነፃ ፈቃዳቸው በትርፍ ጊዜአቸው እንደየሙያቸውና እንደየምርጫቸው በሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ አማካይነት በሰበካው ል ክፍሎች ውስጥ ተመድበው ያገለግላሉ።

ለ) ምእመናንም ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን በማንኛቸውም የሥራ መስኮች እየተሰማሩ የአገልግሎት ድርሻ በነፃ ፈቃዳቸውና በትርፍ የሚገባቸውንና የሚፈለግባቸውን አገልግሎት ማበርከት መብታቸውና ግዴታቸው ነው።

## አንቀጽ ፳

## የሰበካው ቤት ክርስቲያን አገልጋይ ካህናትና ፅ
## ሠራተኞች
## መብትና ግዴታ

፩. መብት፦

ሀ) በሰበካው አስተዳደር ውስጥ የሚያገለግሉት ካህናት
ሠራተኞች እንደየሥራቸውና እንደየሙያቸው በሚሰጡ
መጠን ደመወዝ ማግኘት ሕጋዊ መብታቸው ነው።

ለ) በወር ደመወዝ ለሚከፈላቸው የጡረታ ክፍያቸውን ሳ
ካህናትና ልዩ ልዩ የቤተ ክርስቲያን ሠራተኞች ቤተ
በምትችለው መጠን የጡረታ አበል የማግኘት መብት አ

ሐ) ማናቸውም የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ካህንና ሀ
በሚፈቅደው መሠረት የዓመት ፈቃድና የሕመም
ሠራተኛም የወሊድ ፈቃድ የማግኘት መብት የተጠበቀ

መ) በሙያ፣ በአገልግሎት፣ በሥራ ጥራት፣ በታማኝነትና
የሥራ ውጤት ብቁ ሆኖ ሲገኝ የደረጃና የደመወዝ ዕድ
መብት ይኖረዋል።

ሠ) ከአጥቢያ ቤት ክርስቲያን እስከ መንበረ ፓትርያርክ ጠ
ድረስ በደመወዝ ተቀጥሮ የሚያገለግል ሁሉ በዕድሜ
በጡረታ የሚገለለው የዕድሜው ገደብ ፳ ዓመት (
ሲመላው ነው፤ ነገር ግን ለሥራው ጠቃሚ ሆኖ
ኃላፊው አስተያየት በጡረታ ኮሚቴ ተጣርቶ ለአስተዳደ
ሲወሰንለት የጡረታው ጊዜ ሊራዘምለት ይችላል።

ረ) የጡረታን ጊዜ ለማራዘም ከዚህ በላይ ከተደነገገው
ሕጋዊነት አይኖረውም።

ሰ) ይህ የጡረታ መብት በጊዜያዊነት (በኮንትራት) በአበልና
መልክ በሚከፈል ተመድበው የሚያገለግሉትን አይመለ

ሸ) በሕዝባዊም ሆነ በመንግሥታዊ ድርጅቶች ሲያገለግሉ
የጡረታ መብታቸው የተጠበቀላቸው ግለሰቦች በቤተ ክር
ማለት ከአጥቢያ ቤት ክርስቲያን እስከ መንበረ ፓትርያር
የሥራ መስኮች ለማገልገል በፈለጉ ጊዜ በነፃ ከሚሠሩ በስተቀር
ደመወዝ አይከፈላቸውም፤ ሆኖም ልዩ ሙያ የሚያስፈልግ ሆኖ
ከተገኘ በኮንትራት ተቀጥረው እንዲሠሩ ይደረጋል።

ቀ) ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እስከ መንበረ ፓትርያርክ ድረስ ባሉት
መሥሪያ ቤቶች ተቀጥሮ ሲያገለግል የኖረው ሠራተኛ በሥራው ላይ
እንዳለ ወይም በጡረታ ከተገለለ በኋላ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ
የጡረታ መብቱ ሕግ ለሚፈቅድላቸው ቤተሰቦቹ ይተላለፋል።

በ) ሠራተኛው የጡረታ መብቱ የሚጠበቅለት በቀዋሚ ሠራተኛነት
የጡረታ መዋጮውን እየከፈለ ከአሥር ዓመት በላይ ያገለገለ ሲሆን
ነው፤ የአገልግሎቱ ዘመን ከአሥር ዓመት በታች ከሆነ ግን የሚያ
ገኘው የወር ደመወዝ በአገልግሎት ዘመኑ ልክ ታስቦ አንድ ጊዜ ብቻ
ዳረጎት ይከፈለዋል።

ተ) ሠራተኞች ከአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ወደ ሌላው አጥቢያ ቤተ
ክርስቲያን ወይም ከአንድ መ/ቤት ወደ ሌላ መ/ቤት በሥራ
ተዛውረው ጡረታ በሚወጡበት ጊዜ ለጡረታው አበል አከፋፈል
እንዲያመች ከየደመወዛቸው ያዋጡት ፬% (አራት ከመቶ) የጡረታ
ሒሳብ ታስቦ ጡረታ ወደወጡበት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ወይም
መሥሪያ ቤት ወይም በማዕከል ደረጃ ወደሚቋቋመው ድርጅት ይዛወ
ርላቸዋል።አሠሪው መ/ቤትም ፮% (ስድስት ከመቶውን) ሒሳብ ያሚ
ላላቸዋል።

ቸ) ከመንበረ ፓትርያርክ እስከ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በየደረጃው
በሚገኙት ት/ቤቶች የሚያስተምሩ የትርጓሜ መጻሕፍት፣ የቅኔ(የግዕ
ዝ)፣ የፀዋትወ ዜማ፣ የአቋቋምና የቅዳሴ መምህራን ጉባኤ ዘርግተው
በማስተማር ላይ ከሆኑ የመሥራት ኃይላቸው ሳይደክም በዕድሜ ገደብ
ምክንያት ብቻ በጡረታ እንዳይገለሉ የሥራ መብታቸው የተጠበቀ
ነው።

፪. ግዴታ፦

ሀ) ካህናትና የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ሠራተኞች ለተቀጠሩበት
ሥራ በሙሉ ኃይልና ችሎታ መሥራት ይኖርባቸዋል።

ለ) ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እስከ መንበረ ፓትርያርክ ድረስ ያሉት
ማናቸውም የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ካህናትና ሠራተኞች
ከደመወዛቸው 4%(አራት ከመቶ) የጡረታ መዋጮ ይከፍላሉ።

ሐ) እያንዳንዱ ካህን የንስሐ ልጆች እያንዳንዱ መምህር መንፈሳዊ
ተማሪዎች እንዲኖሩት ማድረግ ግዴታው ነው።

መ) እያንዳንዱ ካህን የንስሐ ልጆቹን የማስተማርና በሰበካ ጉባኤ
የማስመዝገብ፣ የተወሰነውን አስተዋጽኦ በወቅቱ እንዲከፍሉ
የማትጋትና የማስተባበር ኃላፊነት አለበት።

ሠ) ለኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮች ምእመናንና ምእመናት
ከጥምቀት እስከ ጸሎተ ፍትሐት ድረስ አስፈላጊውን መንፈሳዊ

ረ) እያንዳንዱ ካህን ወይም ሠራተኛ በሕገ ቤተ ክርስቲያ የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት ጠብቆ የማስጠበቅ፣ ቤተ ከሚያስነቅፍ የነውር ሥራ ሁሉ መራቅ ግዴታው ነው፡

ሰ) ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እስከ መንበረ ፓትርያርክ ደ ኙት ማናቸውም የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ካህናትና ሠራተኞች እንደ አስፈላጊነቱ ከአንድ አጥቢያ ቤተ ክ( ወደ ሌላ ቤተክርስቲያን ተዛውረው የመሥራት ግዴታ አ

ሸ) ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጀምሮ እስከ መንበረ ፓትር የሚገኙት ማናቸውም የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ካህናት ልዩ ሠራተኞች የተመደቡበትን ሥራ በትክክል የማከና ሥራውን በሚመለከት ጉዳይ ለበላይ ኃላፊ የመታዘዝና ( የመቀበል ግብረገብነትንና ቅን አገልግሎትን የማሳየት ሥ የሥራ ሰዓት የማክበር ግዴታ አለባቸው፡፡

ቀ) በሕመም ወይም በአክል ምክንያት ካልሆነ በቀር ካህን ፈትቶ መቀመጥ የለበትም፡፡ ከእግዚአብሔር በተቀበለው እያንዳንዱ እንደ ስጦታው ማገልገል ይኖርበታል፤ ይል( ምእመናንና ወጣቶችን ከባዕድ ሃይማኖት የመጠበቅና የ ኃላፊነትና ግዴታ አለበት፡፡

በ) የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ዲያቆናት በዲቁና ማዕርጋ ሊቀድሱ (ሊያገለግሉ) የሚችሉት ከአሥር እስከ ሃያ ዓ( የዕድሜ ክልል ነው፤ ዕድሜያቸው ከሃያ ዓመት በላይ ( ሕግ በመወሰን ወይም በድንግልና ለመኖር ቢፈቅዱ ገዳ ሥርዓተ ምንኩስናን ከተቀበሉ በኋላ በማዕርገ ምንኩስና አገልግሎት ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

## አንቀጽ ፳፩

## የሰበካው ቤተ ክርስቲያን ምእመናን መብት(

፩. መብት፦

ሀ) በሰበካው ውስጥ ነዋሪ የሆነ በሰበካ ጉባኤ በአባልነ( የተመዘገበና ሕገ ቤተ ክርስቲያንን ያሟላ፣ መታወቂ( ምእመን ከቤተ ክርስቲያን ለምእመናን የሚገባውን አገልግሎት ማግኘት መብቱ ነው፡፡

ለ) ከነበረበት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚገባውን የከፈለ ( ሌላ ቤተ ክርስቲያን ቢዛወርና መንፈሳዊ አገልግሎት ማግ ተጨማሪ ክፍያ አይጠየቅም፡፡

ሐ) እንግዳ ደራሽና ባይተዋር በሌላ ሰበካ ውስጥ ቢሞት የሰበ ጉባኤ አባልነቱ በመታወቂያ ካርድ ወይም የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታይ መሆኑ በምስክር ከተረጋገጠ የዕለት ጸሎተ ፍትሐት በነፃ ይደረግለታል፡፡

መ) ማናቸውም ምእመን በሰበካ ጉባኤ ተመዝግቦ ወርኃዊና ዓመታዊ አስተዋጽኦውን ከፍሎ መታወቂያና ማስረጃ ያለው ከሆነ በሰበካው የመምረጥና የመመረጥ መብት አለው፡፡

ሠ) በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ተመዝግቦ ተገቢውን አስተዋጽኦ የከፈለ ምእመንና ካስመዘገባቸው ቤተሰቦች መካከል ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ የዕለት ጸሎተ ፍትሐት ያለ ምንም ክፍያ ይፈጸምላቸዋል፡፡

ረ) በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ተመዝግቦና ተገቢውን አስተዋጽኦ ሲከፍል ቆይቶ በቂ ባልሆነ ምክንያት ክፍያውን ለሁለት ዓመት በማቋረጥ የቆየ ምእመን ውዝፉን ብቻ በመክፈል፣ ሳይከፍል የቆየው ከሁለት ዓመት በላይ ከሆነ ከዋናው ክፍያ በተጨማሪ ተገቢውን መቀጫ ከፍሎ ማንኛውንም መንፈሳዊ አገልግሎት የማግኘት መብት አለው፡፡

ሰ) በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ያልተመዘገበና ተገቢውን ወርኃዊና ዓመታዊ አስተዋጽኦ ያልከፈለ ምእመንም ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ የአገልግሎት ዋጋ ከፍሎ ጸሎተ ፍትሐት እንዲደ ርስለት የመጠየቅ መብት አለው፡፡

ሸ) ማንኛውም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባል ከዚህ ዓለም በሞት በሚለይበት ጊዜ በአለበት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጸሎተ ፍትሐት ከተደረገለት በኋላ የመቃብር ቦታ ወደ አለበት ቤተ ክርስቲያን ሲወሰድ የመቃብር ቦታ ማግኘት መብቱ ነው፡፡

፪. ግዴታ፦

ሀ) የሰበካው ምእመናን በገንዘብ አስተዋጽኦ በአስተዳደር፣ በትምህርት፣ በልማትና በማኅበራዊ ኑሮ አገልግሎት በጠቅላላው በሀብት በዕውቀትና በጉልበት በመርዳት በሰበካው ልዩ ልዩ የክፍል ሥራዎች ውስጥ በመሳተፍ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ማገልገል ክርስቲያናዊ ግዴታው ነው፡፡

ለ) ማንኛውም በአንድ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ የሚኖርና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታይ የሆነ ምእመን በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን መመዝገብ፣ በዚህ ደንብ የተወሰነውን አስተዋጽኦ መክፈል፣ የአባልነቱን መታወቂያ መያዝ እንዲሁም ቤተሰቦቹንና ልጆቹን በዝርዝር ማስመዝገብና አካለ መጠን ለደረሱትም በየራሳቸው የአባልነት መታወቂያ እንዲይዙ ማድረግ፣ በሰንበት ት/ቤት የሃይማኖት ትምህርት እንዲከታተሉና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን እንዲጠብቁ የማድረግ ግዴታ አለበት::

ሐ) ማንኛውም ምእመን ሕገ ቤተ ክርስቲያንን የሚተላለፍ፣ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ነቅፎ የሚያስነቅፍ ክብረ ቤተ ክርስቲያንን ደፍሮ የሚያስደፍር መሆን የለበትም፤ በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት፣

በቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት መመራትና የምእመንነት ደረጃ ጸንቶ መኖር ግዴታው ነው::

መ) አንድ ምእመን ከሚኖርበት የአጥቢያ ቤተ ክርስቲ
ምክንያት ወደ ሌላ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰ
ከነበረበት ሰበካ ጉባኤ የተቀበለውን የአባልነት መታ
በኋላ የመሸኛ ደብዳቤ መቀበልና ለተዛወረበት ሰ
ጉባኤ በወቅቱ አቅርቦ መመዝገብ ይኖርበታል::

ሠ) አንድ ምእመን በሰበካው ቤተ ክርስቲያን የሰበካ ሰ
አባላትን የመምረጥ መብት እንዳለው ሁሉ የመመረ
ግዴታም አለበት::

ረ) እያንዳንዱ ምእመን ሥልጣነ ክህነት ካላቸው ቀሳ
አንዱን መርጦ በንስሐ አባትነት መያዝ መንፈ
ነው::

## አንቀጽ ፷፪

## የአገልጋይ ካህናትን ብዛት ስለመወ

በገዳማት፣ በአድባራትና በገጠር አብያተ ክርስቲያ
የሚያገለግሉት ካህናት ልዩ ልዩ ሠራተኞች ብዛት እንደየአገል
መጠን ከቅዱስ ሲኖዶስ በሚሰጠው መመሪያ ይወሰናል::

## አንቀጽ ፷፫

## ይህንን ቃለ ዓዋዲና ሕገ ቤተ ክርስቲያን በሚተላለፍ ላይ የሚሰጥ ውሳኔ

፩. ማንኛውም የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ካህን ወይም ሠራተኛ
ዓዋዲ በአንቀጽ ፷ በንዑስ አንቀጽ ፪ የተደነገገውን ተላል
እንደጥፋቱ ሁኔታ በመጀመሪያ ምክርና ተግሣጽ፣ በሁለተኛ
ይሰጠዋል፤ በሦስተኛ ጊዜ ቅጣት ይወሰንበታል፤ ቅጣቱም እ
ክብደት ተመዛዝኖ በገንዘብ ወይም በቀኖና፣ ከሥራ በማዛወ
በማገድ፣ ከሥራ በማሰናበት ወይም ከአባልነት በማግለል ሊ
ሆኖም የመጨረሻው ውሳኔ ማለት ከሥራ የማሰናበቱ ወይም
የማግለሉ ቅጣት ሊጸና የሚችለው የወረዳው ቤት ክህነት ተ
ወደ መንበረ ጵጵስናው ቀርቦ የጸደቀ እንደሆን ነው::

፪. አንድ ካህን ወይም ሠራተኛ ከሥራው እንዲሰናበት ወይም
እንዲታገድ የሚሰጠው ውሳኔ ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው፦

ሀ) በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንና በወረዳ ደረጃ ከሆነ የሀ/ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ በአስተዳደር ጉባኤ አይቶ ሲያጸድቀው፣

ለ) ከሀ/ስብከት ጀምሮ ባሉት የሥራ ዘርፎች የተመደበ ሠራተኛ ከሆነ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ በጠቅላይ ቤተ ክህነት አስተደደር ጉባኤ አይቶ ሲያጸድቀው ብቻ ነው::

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ምክርና ተግሣፅ እንዲሁም ማስጠንቀቂያ ከተሰጠው በኋላ አንድ ካህን የንስሐ ልጁን በሰበካ ጉባኤ ሳያስመዘግብ ወርኃዊና ዓመታዊ አስተዋጽኦውን እንዲከፍል ሳያደርግ ሌሎችንም መንፈሳዊ ግዴታዎች ሳይፈጽምና ሳያስፈጽም ቆይቶ የንስሐ ልጁ ሲሞት ለፍትሐት ብቻ የሚያቀርብ ከሆነ፦

ሀ) ከመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ጋር የአንድ ወር ግማሽ ደመወዙን፣
ለ) በሁለተኛ ጊዜ የአንድ ወር ሙሉ ደመወዙን ይቀጣል::
ሐ) በሦስተኛ ጊዜ ከሥልጣነ ክህነቱ ይታገዳል::

፬. አንድ ምእመን መንፈሳዊ ግዴታውን መወጣት ካልቻለና በዚህ ቃለ ዓዋዲ አንቀጽ ፷፩ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተደነገገውን ተላልፎ ቢገኝ፦
   ሀ) በመጀመሪያ ጊዜ በንሥሐ አባቱ ወይም በቤተ ክርስቲያኑ በተወከለ አባት አማካይነት ምክርና ትምህርት
   ለ) በሁለተኛ ጊዜ ተግሣጽና ቀኖና ይሰጠዋል፡፡
   ሐ) በሦስተኛ ጊዜ ከማስጠንቀቂያ ጋር ለተወሰነ ጊዜ ከአባልነቱ እንዲታገድ ይሆናል፡፡

፭. አንድ ምእመን ከአባልነት እንዲሠረዝ የሚተላለፈው ውሳኔ ሊፀና የሚችለው የሀ/ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ በልዩ ጉባኤ አይቶ ሲያጸድቀው ብቻ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ ፷፬

## የአፈጻጸም ሥነ ሥርዓት

፩. በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ(ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ) በተሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ያለው ቢኖር ጉዳዩ ደረጃውን ጠብቆ ለወረዳው ቤተ ክህነት በይግባኝ ሊቀርብ ይችላል፡፡
፪. በወረዳው ቤተ ክህነት የተሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ካስከተለ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ በተገኘበት በሀገረ ስብከቱ አስተዳደር ጉባኤ ታይቶ ይወሰናል፡፡
፫. ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጀምሮ እስከ ወረዳው ያሉት የሰበካ ጉባኤያት አባላት ተመርጠው ሥራ ከጀመሩ በኋላ ገንዘብ ቢያጠፉ ወይም ሌላ ችግር ቢፈጥሩ የመንበረ ጵጵስናው ሀገረ ስብከት አስተዳደር ጉባኤ በሊቀ ጳጳሱ ሰብሳቢነት ተመልክቶ የመሻር ሥልጣን አለው፡፡
፬. በመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት የተመረጡት የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ (ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ)አባላት የአሠራር በደል ወይም ፈጽመው ቢገኙ በጠቅላይ ቤተ ክህነት አስተዳደር ጉባኤ ታይ በምትካቸው ሌሎች አባላት ይተካሉ፡፡
፭. ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጀምሮ በየደረጃው የሚገኙት የሰበ ውያን ጉባኤያት የሒሳብ አያያዝና የንብረት አጠባበቅ በማዕከ በጠቅላይ ቤተ ክህነት እየተዘጋጁ በሚወጡት ካርኒዎችና መገ መሥራት ግዴታ ሲሆን ከዚህ ውጭ በሌላ ካርኒ ሲሠሩ የተገ ይጠየቃሉ፡፡
፮. ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ለመጠበቅ የአገልጋዮቿን ካህናት ነ ሻልና ለልጆቿ ምእመናን የሚሰጠውን መንፈሳዊና ማኅበራዊ ለማሟላት የወጣውን ይህን ቃለ ዓዋዲና ሕገ ቤተ ክርስቲያን እንዳይውል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚቃወሙ ካ ቢነታቸው ምእመናን ከአባልነታቸው ይሰረዛሉ፡፡
፯. ከአሁን በፊት ሚያዝያ ፲፱ ቀን ፲፱፻፸ ዓ.ም. የወጣው ቃ ታኅሣሥ ፲ ቀን ፲፱፻፸፬ ዓ.ም. የወጣው የቃለ ዓዋዲ ማሻሻ ግንቦት ፱ ቀን ፲፱፻፸፮ ዓ.ም. የወጣው የሰበካ መንፈሳዊ ጉባ ደንብና በየጊዜው የተላለፉት መመሪያዎች ሁሉበዚህ ቃለ ዓዋ

## አንቀጽ ፷፭

## የቃለ ዓዋዲው መሻሻል

ይህ ቃለ ዓዋዲ ወደፊት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በቅዱስ ሲ ትእዛዝ እንደገና ሊሻሻል ይችላል፡፡

## አንቀጽ ፷፮

## ቃለ ዓዋዲው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ቃለ ዓዋዲ በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ጸድቆ ከወጣበት ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
ቅዱስ ሲኖዶስ
አዲስ አበባ ግንቦት ፲ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም.